# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 214 ሚያዝያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

# ለአገርና ለሕዝብ የሚተርፍ ትውልድ
## ለመገንባት ሁሉም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሲወጣ ይገባል

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- አገሩን የሚወድ፣ በውይይት የሚያምን፣ ለሕዝቡ ሕይወት መለወጥ የሚሠራ፣ ጠንካራ የሥራ ባህል ያለው እና ሥነ ምግባር የተላበሰ ትውልድ ለመቅረጽ ከትምህርት ተቋማት ጎን ለጎን ሁሉም ወገን የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት እንደሚኖርበት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገለጹ።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አዘጋጅነት «የመደመር ትውልድን መቅረጽ» በሚል ርዕሰ ጉዳይ ትናንት በወዳጅነት አደባባይ በተካሄደው አዲስ ወግ ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ ዛሬ በአገሪቱ የሚታዩ ችግሮቹ ሁሉ መነሻቸው የተለያየ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን ከትምህርት ሥርዓቱ የሚመነጩ ናቸው። አዲሱን ትውልድ አገሩን የሚወድ፣ ለሕዝቡ ሕይወት መለወጥ የሚሠራ፣ ጠንካራ የሥራ ባህል ያለው እና ሥነ ምግባር የተላበሰ ለማድረግ ከትምህርት ተቋማት ጎን


ለአገርና ለሕዝብ የሚተርፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ሥልጠናው የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን ለማሳደግ ትልቅ አቅም የተገኘበት መሆኑ ተገለጸ

- ኢፕድ ውጤታማ የዘርፉ ሥልጠናዎችን እያቀረበ ይገኛል


ገጽ 4




«የልዩ ኃይል ሪፎርም የሚካሄደው የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያረጋግጥ፣ የአገርን አንድነት የሚያጸና ጠንካራ የጸጥታ ኃይል ለመገንባት ነው»

- አቶ ግርማ የሺጥላ
የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ


ገጽ 4


# ኢትዮጵያን ማስቀጠል ያስቻሉ ማህበራዊ እሴቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- እስካሁን ኢትዮጵያን ማስቀጠል ያስቻሉ ማህበራዊ የአኗኗር ዘይቤዎችና መልካም ጉርብትናን የመሰሉ ማህበራዊ እሴቶችን ማጠናከር እንደሚስፈልግ ተገለጸ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አዘጋጅነት «የሀሳብ መዋጮ» በሚል ይዘት «ትንሳኤ ለእሴቶቻችን!!!» በሚል ርዕስ የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በውይይት መድረኩ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው እንደገለጹት፣ እሴቶቻችን የአገር ምሰሶና ካስማ ናቸው።


ኢትዮጵያን ማስቀጠል ያስቻሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ - ሐዲስ አብርሃ






አቶ ሃብታሙ ታዬ

# በፆም ምክንያት የደም ለጋሾች ቁጥር መቀነሱ ተገለጸ

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- የፆም ወቅት በመሆኑ ምክንያት የደም ለጋሾች ቁጥር መቀነሱ ሕይወት ለማትረፍ የሚደረገውን ጥረት እንዳያስተጓጉለው ሥጋት መፍጠሩን የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክርስትና እና በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የፆም ወቅት መሆኑ የደም ለጋሾችን ቁጥር ቀንሶታል። የደም ለጋሾች ቁጥር በፆም ምክንያት መቀነሱም ሕይወት ለማትረፍ የሚደረገውን ጥረት እንዳያስተጓጉለው ሥጋት ፈጥሯል።

ከፆሙ በፊት በቀን እስከ 350 ዩኒት ደም መሰብሰብ ይቻል እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሃብታሙ፤ አሁን ግን በሥራ ቀናት ማለትም ከሰኞ እስከ አርብ ባለው ጊዜ በቀን ከ240 ዩኒት ያልበለጠ ደም ነው መሰብሰብ የተቻለው ብለዋል።

ቅዳሜና እሁድ ላይ የተሻለ መሆኑን ጠቁመውም፤ በቀን 330 ዩኒት ደም መሰብሰብ መቻሉን አንስተው፤ «በአዲስ አበባ በቀን 400 ዩኒት የሚጠጋ ደም ያስፈልጋል።» ሲሉ ገልጸዋል። የሰው ሕይወት ለመታደግ የሚያስፈልገውን ያክል ደም መሰብሰብ ይኖርበታልም ሲሉ አሳስበዋል።

በሕክምና ሥራ ውስጥ ደም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሃብታሙ፤ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችም አሁን ላይ እየጨመሩ መምጣታቸውን በማንሳት ይህ የደም ፍላጎቱን እንደሚጨምረው አብራርተዋል።

የደም ካንሰር ከመባባሱ ጋር ተያይዞ ሕክምናውን የሚሰጡ ተቋማትም እየሰፉ መምጣታቸውን እንደ አብነት በማንሳት፤ በዚህም እንደ አገር 561 የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የደም ካንሰር ሕክምና እየተሰጠ ይገኛል። ስለዚህ የደም አቅርቦቱም በዚያው ልክ መሆን አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

አሁን ላይ የሚያስፈልገውን ደም ለመሰብሰብ በሥራ ቀናት በመንግሥት መስሪያቤቶች፣ በሃይማኖታዊ ቦታዎች እና በትምህርት ቤቶች በመዘዋወር የደም መሰብስብ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ጎን ለጎንም በአዲስ አበባ ከተማ በአደባባዮች ድንኳን በመትከል የበጎ ፍቃደኛ ደም ለጋሾችን የመቀስቀስ ሥራ ለመሥራት አቅደናል ብለዋል።

ኅብረተሰቡ በፆም ወቅት ደም መለገሱ ጉዳት እንደሌለው ተገንዝቦ ከፆም ሰዓት እና ከአፍጥር በኋላ ደም በመለገስ የወገኑን ሕይወት መታደግ ይኖርበታል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# «ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ የሚሆኑት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጤናማ ሲሆን ነው»

- ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ
የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

በኃይሉ አበራ



ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- ሠራተኛውና አሠሪው ለዓላማቸው ጸንተው ውጤት የሚያመጡት እና ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ የሚሆኑት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጤናማ ሲሆን ነው ሲሉ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገለጹ። አቢሲኒያ ሽልማት ድርጅት ለ50 ተቋማትና ትጉሃን ሠራተኞች የመጀመሪያውን የኢንዱስትሪ ሽልማት ሰጥቷል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ፣ የከፍተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በመምረጥ ሽልማቱን በማሰናዳቱና ማህበራዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣቱ የአቢሲኒያ ሽልማት ድርጅት ፕሬዚዳንትን ጨምሮ ሠራተኛውንና አመራሩን አመሥግነዋል።

በተለይ ከሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያ ለወጣቶች እና ሴቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አንጻር ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ኢንዱስትሪው መሆኑን ጠቁመው፣ ለአገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ የሚገኝ ሴክተር በመሆኑ አቢሲንያ የጥራት ሽልማት ዘርፉን ማየቱ ተገቢነት ያለው ነው ብለዋል።

«የአሠሪና ሠራተኛው ስኬትም የተቋማት ስኬት ነው፤ ሽልማቱን ማግኘታችሁ ለቀጣይ ትልቅ ኃላፊነት ጭምር ነው» ያሉት ዶክተር ኤርጎጌ፤ በቀጣይም የሥራ ዕድል በመፍጠር ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ሌሎች ተሸላሚዎችን ማፍራት የሚጠበቅ ነው ሲሉም አሳስበዋል።

የአቢሲኒያ ሽልማት ድርጅት የቦርድ ሰብሳቢ አቶ አሰፋ ከሲቶ፥ ድርጅቱ «ዓለምንና ሕዝቦቿን የሚታደግ የላቀ ሥራ ለሠሩ ትጉኃን እንሸልማለን» በሚል መሪ ቃል በግለሰብ ደረጃ፣ በሕብረትና በተቋማት ደረጃ የተሠሩ ሥራዎችን በመመዘን የሚሸልም ተቋም ነው ብለዋል።

የኢንዱስትሪ ሽልማት ሁሉንም የኢንዱስትሪ ክፍሎች የያዘ፣ የሠራተኛውን ክፍል ያካተተ፣ የሥራ መሪዎችንና የግልና የመንግሥት ተቋማትን ያቀፈ መሆን አለበት ያሉት አቶ አሰፋ፤ በዚህ መሠረት ድርጅቱ በአገራችን ያለውን የኢንዱስትሪ አጠቃላይ እንቅስቃሴ በማጤን ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ ደረጃ የኢንዱስትሪ ሽልማት ለመሸለም ሲያጠና መቆየቱን አስታውሰዋል።

በአገራችን ታሪክ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት እና በደርግ ዘመን የወርቅ ሜሪኩሪ ሽልማት ከመካሄድ በዘለለ ግልጽና ወጥነት ያለው ኢንዱስትሪ ሽልማት አለመካሄዱን ተናግረዋል።

በመሆኑም የላቀ ሥራ ለሠሩና ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት የሚከተሉ ተቋማትን በመሸለም ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት ለማህበረሰብ የሚያቀርቡ ሙያተኞችና ተቋማትን በመፍጠር ለአገር ሁለንተናዊ እድገት ለማስመዝገብ ሽልማቱ ጠቃሚ መሆኑን ጠቁመዋል።

ሽልማቱም አገልግሎት አሰጣጣቸውና ምርታቸውን መሠረት በማድረግ ተቋማዊ ውጤታቸው ላይ ከ2009-2014 በተደረገ ውጫዊ ምዘና በ24 መሠረታዊ መለኪያዎች አዳዲስና ዘመናዊ አሠራር የዘረጉ፣ የላቀ እድገት ላስመዘገቡ ነውም ብለዋል።

የኢንዱስትሪ ሽልማት ሁሉንም የኢንዱስትሪ ክፍሎች የያዘ፣ የሠራተኛውን ክፍል ያካተተ፣ የሥራ መሪዎችን እና የግልና የመንግሥት ተቋማትን ያቀፈ መሆን ስለሚገባው ድርጅቱ ሁሉን አቀፍ የኢንዱስትሪ ሽልማት በመደበኛ ሽልማት የሰጠ መሆኑንም አስታውሰዋል።

አቢሲኒያ የሽልማት ድርጅት በኢንዱስትሪ ዘርፍ እሁድ ዕለት ባካሄደው ሁለተኛ ዙር የከፍተኛ ክብር ሽልማት መርሀ ግብሩም ለ25 ተቋማት እና የተቋማቱ ትጉኃን ሠራተኞች ሜዳሊያና ዲፕሎማ ሸልሟል።

የአበባ ባልትና፣ አዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት፣ አዲስ ኢሜጂንግ፣ አደይ አበባ ብዙኃን ትራንስፖርት እና አዲስ አድማስ ዩኒቨርሲቲ፣ AE ኬሚካልስ፣ አጋር ማይክሮ ፋይናንስ፣ በርታ ኮንስትራክሽን፣ ሰበታ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ቤንች ማጂ ጫካ ቡና እና ቦራ ፋርምስ ጨምሮ በጠቅላላው 25 ተቋማትና ትጉሃን ሠራተኞች ሜዳሊያና ዲፕሎማ ሸልሟል።

# ሆስፒታሉ በአንድ ዓመት ለ109 ታካሚዎች የቃጠሎ ሕክምና ሰጥቷል

በዳግማዊት ግርማ



አዲስ አበባ፡- በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለ109 ታካሚዎች የቃጠሎ ሕክምና መስጠቱንና አብዛኛዎቹ ታካሚዎች ሕፃናት መሆናቸውን የአርባምንጭ አጠቃላይ ሆስፒታል ገለጸ። የሚጥል በሽታ ታማሚዎችና ነዳጅ ቸርቻሪዎች ለእሳት ቃጠሎ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸው ተጠቁሟል።

በአርባምንጭ አጠቃላይ ሆስፒታል የፕላስቲክና ሪኮንስትራክቲቭ ቀዶ ሕክምና ክፍል ሀኪም ዶክተር ኤፍሬም ጋሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአርባምንጭ አጠቃላይ ሆስፒታል ባለፉት ሦስት ዓመታት በእሳት አደጋ ለተጎዱ 195 ታካሚዎች ሕክምና ሰጥቷል። ከዚህ ቁጥር ውስጥ 109 ታካሚዎች በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ሕክምና ማግኘት የቻሉ ናቸው።

ሆስፒታሉ በሦስት ዓመታት ውስጥ ካከማቸው ታካሚዎች 137ቱ ከ14 ዓመት በታች ሕፃናት መሆናቸውንም ዶክተር ኤፍሬም ገልጸዋል።

አብዛኛው የቃጠሎ ታካሚዎች ሕፃናት መሆናቸውን ያመላከቱት ዶክተር ኤፍሬም፤ የልጆች አያያዝ ላይ የሚፈጠረው ክፍተት የተጋላጮች ቁጥር እንዲያሻቅብ ማድረጉንም ነው የተናገሩት።

ሕክምናው በኅብረተሰቡ ዘንድ የአሳሳቢነቱን ያህል ትኩረት አልተሰጠውም ያሉት ዶክተር ኤፍሬም፤ የቃጠሎ ሕክምና ከቁስል በተጨማሪ በታማሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ ስቃይን የሚያስከትል ስለሆነ በተቋማት ከሚሰጠው ሕክምና ጎን ለጎን የሥነልቦና ድጋፍ ላይም ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባውም አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች በተሠሩ ጥናቶች መሠረት ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚከሰቱ የቃጠሎ አደጋ የሚደርሱት በቤት ውስጥ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ኤፍሬም፤ ከእሳት አደጋዎች መከሰቻ ምክንያቶች ውስጥም የፈላ ውሃ፣ ሻይና ወጥ ጥቂቶቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ዶክተር ኤፍሬም በንግግራቸው፤ የሚጥል በሽታ ታማሚዎችና ነዳጅ ቸርቻሪዎች ለእሳት ቃጠሎ ተጋላጭነታቸው እንዲሁም በሰውነታቸው ላይ የሚያደርሰው ጉዳትም ከፍተኛ መሆኑን በመግለፅ፤ እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለየ መልኩ ራሳቸውን እንዲጠብቁ አሳስበዋል።

የሚጥል በሽታ ታማሚዎች ድንገት ጥሏቸው እሳት ዳር በሚወድቁበት ወቅት እጅና እግር መቆረጥና ሌሎችንም ጉዳቶች እንደሚደርሱባቸው የገለጹት ዶክተር ኤፍሬም፤ በሽታውን መከላከል የሚቻል በመሆኑ የቃጠሎ ጉዳት ሳይደርስ መከታተል እንደሚያስፈልግም ነው የተናገሩት።

የቃጠሎ ሕክምና ከቁስል ባሻገር በታማሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ ስቃይን የሚያስከትል ስለሆነ ከሥነልቦና ችግር አንፃር ሰዎችን ከሰው ተለይተው እንዲኖሩ የሚያደርግና ኢኮኖሚያዊ ጫናውም ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ኤፍሬም፤ መገናኛ ብዙኃንም የግንዛቤ መፍጠር ሥራ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉም ምክራቸውን ለግሰዋል።

በአርባ ምንጭ ሆስፒታል ቃጠሎ ሕክምና ክፍል ከሦስት ዓመታት በፊት በክፍል ደረጃ የተዋቀረ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት እንደማንኛውም ታካሚ አንድ ላይ እንደሚታከሙ የጠቀሱት ዶክተር ኤፍሬም በአሁኑ ወቅትም ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለሚመጡ ታካሚዎች ሕክምናውን እንደሚሰጥም ጨምረው ገልጸዋል።

# የነዳጅ ግብይትን ስለማዘመን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንዲያደርጉ ተጠየቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የነዳጅ ግብይትን ለማዘመንና ሥርዓቱን ለማስተካከል ለሚደረገው ጥረት መሳካት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሚኒስቴር መስሪያቤቶቹ አሳሰቡ።

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ኢትዮ ቴሌኮም በነዳጅ ግብይት ሪፎርም ትግበራና ግብይቱን በኤሌክትሮኒክስ ማከናወን ላይ ያተኮረ ውይይት ከባለድርሻ አካላት ጋር አካሂደዋል።

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትሩ ዶክተር ዓለሙ ስሜ በምክክር መድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ የነዳጅ ግብይቱን ማዘመን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር የሚገባውን ነዳጅ ግብይት ሥርዓት በማስተካከል የሕዝብን እንግልት ለማቃለልና የሕዝብንና የመንግሥትን ሀብት ከብክነት ለመከላከል ያስችላል።

የነዳጅ ግብይቱን በኤሌክትሮኒክስ አማራጮች ማድረግ ትልቅ የለውጥ ሥራ በመሆኑ የአመራር ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ ሥርዓቱ በአግባቡ እንዲተገበር የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ድጋፍ፣ ክትትልና ቁርጠኝነት ይጠይቃል ብለዋል።

መንግሥት በከፍተኛ ወጪ ድጎማ የሚያደርግለት ነዳጅ በሕገወጦች ምክንያት ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል እየተደረገ መሆኑን አስታውሰው፤ በቀጣይነት ግብይቱን ከመቆጣጠር ባለፈ ተሽከርካሪዎችን መቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት እንደሚዘረጋም ጠቁመዋል።

ለሥራው መሳካት ክልሎችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ መገናኛ ብዙኃንም በጉዳዩ ላይ ግልጽነት በመፍጠር በኩል የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ አሳስበዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ አቶ ገብረመስቀል ጫላ በበኩላቸው፤ ከሰኔ 28 ቀን 2014 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገው የነዳጅ ግብይት ሪፎርም ጥሩ ውጤት እያስመዘገበ ነው ብለዋል።

የነዳጅ ግብይት ሪፎርሙ ሲጀመር ነዳጅ መሸጥ ከነበረበት ከግማሽ በታች በሆነ ዋጋ በከፍተኛ ድጎማ ለገበያ ይቀርብ ነበር። አሁን ላይ ያለው የድጎማ ዋጋና መሸጥ ከነበረበት ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት አስር ብር የሚጠጋ ብቻ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

የነዳጅ ግብይት ሪፎርም መጀመር የመንግሥት ዕዳ እየቀነሰ እንዲመጣ አድርጓል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሚደረገው ድጎማ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል እያደረገ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ከቤንዚል በስተቀር ያለው የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ከጎረቤት አገራት ጋር እንዲቀራረብ በማድረግ የነዳጅ ኮንትሮባንድ እንዲቀንስ ማድረግ መቻሉንም አብራርተዋል።

በቀጣይነትም በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በሂደት ከድጎማ ሥርዓት በመውጣት ወደነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ አስተዳደር ለመመለስ ይሠራል ብለዋል።

መንግሥት የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረበት ሰኔ 2014 ዓ.ም ጀምሮ 9ነጥብ8 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉን ያመለከቱት አቶ ገብረመስቀል፤ ድጎማውን በአግባቡ ለኅብረተሰቡ እንዲደርስ በማድረግ በኩል ችግሮች ተስተውለዋል ሲሉም ጠቅሰዋል።

ግብይቱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መከናወኑም ፍትሃዊ የነዳጅ ስርጭትና አጠቃቀም እንዲኖርና የሀብት ብክነትና ሌብነትን ለመቆጣጠር ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

በመሆኑም ነዳጅ ማደያዎች፣ አሽከርካሪዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የየድርሻቸውን ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ቺፍ ሞባይል መኒ ኦፊሰር አቶ ብሩክ አድሃና እንዳሉት ደግሞ፤ ኢትዮ ቴሌኮም እስካሁን ድረስ ለታለመለት ነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚዎች አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።

በቀጣይነትም ያለውን ሰፊ ተደራሽነት ተጠቅሞ ሁሉም ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ግብይቱን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲፈጽሙ ለማስቻል አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጓል ብለዋል።

የነዳጅ ኤሌክትሮኒክስ ግብይት ከዚህ በፊት በድጎማ ተጠቃሚዎች ላይ ሲተገበር የቆየ ሲሆን፤ ከሚያዝያ 16 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ሙሉ በሙሉ ይተገበራል። ከግንቦት አንድ ቀን 2015 ጀምሮ ዓመታዊ ኩፖን ከገዙ ደንበኞች በስተቀር በመላ አገሪቱ ግብይቱ በአስገዳጅነት በኤሌክትሮኒክስ አማራጮች እንደሚደረግ የተገለጸ ሲሆን፤ ከሐምሌ አንድ 2015 ጀምሮ ግብይቱ በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ አማራጮች ብቻ እንደሚከናወን ተጠቁሟል።



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

# በቀጣናው የሚከሰቱ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር ያለመ ስብሰባ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በምሥራቅ አፍሪካ የሚከሰቱ የሽብርተኝነትና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል ስብሰባ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው።

በኢትዮጵያ የወንጀል ምርመራ ዳይሬክተር ምክትል ኮሚሽነር ዘላለም መንግስቴ በስብሰባው መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ ስብሰባው የወንጀል ምርመራ ሥራዎችን በጋራ ለመሥራትና መረጃ ለመለዋወጥ ያስችላል። በዚህም በቀጣናው የሚስተዋለውን ሽብርተኝነትና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው።

በስብሰባው ላይ የምሥራቅ አፍሪካ 14 አገራት የወንጀል ምርመራ ቢሮ ኃላፊዎች በመሳተፍ ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህም በቀጣናው የሚስተዋሉትን ድንበር ዘለል ወንጀሎች በጋራ ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው ብለዋል።

እንደ ምክትል ኮሚሽነር ዘላለም ገለጻ፤ የስብሰባው ዓላማ በቀጣናው የሚስተዋለውን የሽብርተኝነትና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በጋራ ለመቆጣጠር ያለመ ነው። በተለይም በሳይበር የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ከኢንተርፖል ጋር በመቀናጀት ለመከላከል በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ምክክር ይካሄዳል።

ኢትዮጵያ ለቀጣይ ሁለት ዓመታት በሊቀመንበርነት የምትመራው ዘርፍ መሆኑን በመጥቀስም፤ በአባል አገራቱ የጋራ ቅንጅትን በመፍጠር በቀጣናው የሚስተዋሉ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች ላይ በትኩረት እንደሚሠራ አስረድተዋል።

በቀጣዩ መርሃግብር በጾታ፣ በሳይበር፣ በሽብርተኝነት በሚፈጸሙ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች ላይ የመወያያ ጽሑፎች ቀርበው ምክክር ይካሄድባቸዋል ብለዋል።

የብሔራዊ ኢንተርፖልና ዓለም አቀፍ የፖሊሶች ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኮማንደር ጸጋዬ ኃይሌ በበኩላቸው፤ ስብሰባው የቀጣናው የፖሊስ አዛዦች ስብሰባ ላይ የተቀመጡ አቅጣጫዎች የሚገመገሙበት እና በቀጣይ በሚካሄደው የፖሊስ አዛዦች ህብረት ስብሰባ ሪፖርት የሚቀርብበት ነው።

ጉባኤው በሦስት ቀናት ስብሰባው የተለያዩ የመወያያ ሰነዶች ቀርበውለት የሚወያይበት መሆኑን ገልጸው፤ በአባል አገራቱ መካከል በከብቶች ዝርፊያ ዙሪያ የውሳኔ ሀሳቦችን አፈጻጸም የሚገመገም መሆኑን ገልጸዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ የምርመራ ፖሊስ አዛዦች ጉባኤ ላይ ቡሩንዲ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ሩዋንዳን ጨምሮ አስራ አራት የአባል አገራት በመሳተፍ ላይ ሲሆኑ፣ ስብሰባው ለሦስት ቀናት የሚቆይ ነው።

# በከተማዋ በሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ቁጥጥር እየተደረገ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በከተማዋ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ለኅብረተሰቡ የሰብል ምርቶችን በምን ያህል ዋጋ እንደሚሸጡና የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር በተለያዩ ክፍለከተሞች በመዘዋወር ቁጥጥር እያደረገ መሆኑን አስታወቀ። ቢሮው ሁለት ሺህ 700 ኩንታል ጤፍ ከኦሮሚያ ክልል ተረክቧል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በከተማዋ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች የጤፍ፣ የዱቄት እና ለዕለት ተዕለት የሚውሉ ምርቶችን ለኅብረተሰቡ በምን ያህል ዋጋ እንደሚሸጡና ምን ያህል ክምችት እንዳላቸው እንዲሁም ከበዓል ጋር ተያይዞ የአቅርቦት እጥረት እንዳይፈጠር የመስክ ምልከታ አድርገዋል።

በዚህም የሸማች ማህበራትና ዩኒየኖች ምርቶቹን ለኅብረተሰቡ ከበፊቱ ቅናሽ ባለው መልኩ እያከፋፈሉ ነው ያሉት የቢሮው ኃላፊ አቶ ቢኒያም፤ በከተማዋ ከፍተኛ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲኖር ከኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ጋር በጋራ እየሠራን ነው ብለዋል፤ ካለፉት ሦስት ሳምንታት ጀምሮ የኦሮሚያ ክልል ምርቶችን በስፋት ሲያቀርብልን ቆይቷል። ለዚህም በቢሮው እና በነዋሪው ስም ክልሉን እናመሰግናለን ብለዋል።

ከኦሮሚያ ክልል ሁለት ሺህ 700 ኩንታል ጤፍ ተረክበናል ያሉት አቶ ቢኒያም፤ ይህም ለ11ዱ ክፍለከተሞች እየተከፋፈለ ይገኛል። በዓሉን በማስመልከትም ተጨማሪ ሦስት ሺህ ኩንታል ጤፍ ለክፍለከተሞች ይከፋፈላል ብለዋል።

አቶ ቢኒያም አክለውም፤ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ አካላት ከድርጊታቸው ሊታቀቡ ይገባል። ነጋዴውም ምርቶችን ለኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ለአገሩ የሚጠበቅበትን አስተዋጽዖ ማድረግ አለበት። በከተማዋ ሰው ሠራሽ የአቅርቦት ችግር ለመፍጠር የሚጥሩ አካላት ላይ እርምጃ ይወሰዳል። ቢሮው በከተማዋ የአቅርቦት ችግር እንዳይኖር ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ብለዋል።

የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳንኤል ቸርነት በጤፍ ርክክቡ ወቅት እንደተናገሩት፤ ካለፉት ሦስት ሳምንታት ጀምሮ የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ጋር ከ62 ሺህ ኩንታል በላይ የገበያ ትስስር አድርጓል። ከዚህም 35 ሺህ ኩንታል የሚጠጋው ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ትስስር ተደርጎ የተከፋፈለ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ምርቶች ደግሞ በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች ጊዜያዊ መሸጫ ቦታዎች ምርቱን ሕዝቡ በቀጥታ እንዲያገኝ ተደርጓል።

የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ በከተማዋ የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር ከምን ጊዜውም በላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የምርት ርክክብ የተደረገው በጎፋ መጋዘን ሲሆን የቁጥጥር ሥራው ደግሞ በኮልፌ እና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ነው። ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ ጠቁመዋል።

# ሥልጠናው የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን ለማሳደግ ትልቅ አቅም የተገኘበት መሆኑ ተገለጸ

## - ኢፕድ ውጤታማ የዘርፉ ሥልጠናዎችን እያቀረበ ይገኛል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዳማ፡- «ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና» የተሰኘው ሥልጠና የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚረዳ ትልቅ አቅም የተገኘበት ነው ሲሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ዴሲሳ አስታወቁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎችን ክህሎት ለማሳደግ በሚረዱ ሥልጠናዎች ውጤታማ ሥራ ማከናወን እንደቻለ አቶ ከበደ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከል ከመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር ያዘጋጀውና ላለፉት 4 ቀናት ሲካሄድ የቆየው «ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና» የተሰኘው ሥልጠና ትናንት ተጠናቋል።

በማጠቃለያ መርሃ ግብሩ ላይ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ዴሲሳ እንደገለጹት፤ በአገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የተቃኘ የኮሙኒኬሽን ሥራ ለማከናወን የሚረዳ ውጤታማ ሥልጠና መሰጠቱን ተናግረዋል።

አቶ ከበደ እንደገለጹት፤ የኮሙኒኬሽን ሙያተኞች በሚያከናውኗቸው ሥራዎች ሕብረብሔራዊ አንድነትን የሚያሰርጹ ክንውኖች ያስፈልጓቸዋል። በዚህ ረገድ ምን ዓይነት ተግባራዊ ሥራ ማከናወን ይቻላል የሚለውን ያመላከተ ሥልጠና በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያ በአገር ግንባታ ላይ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይሄን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡና ሙያዊ አቅማቸው እንዲጎለብት የሚያግዝ ሥልጠና መሰጠቱን ተናግረዋል።



አቶ ከበደ ዴሲሳ

ፎቶ - ዳኜ አበራ

በተጨማሪ በተለያዩ ክልልና የፌዴራል የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያዎች መካከል ትስስር መፍጠር የቻለ ሥልጠና መሆኑን ጠቁመዋል።

ለኮሙኒኬሽን ሥራዎች ውጤታማነት ትልቅ አቅም የተገኘበት በመሆኑ ተመሳሳይ ሥልጠናዎች በቀጣይም ይከናወናሉ ሲሉ አቶ ከበደ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎችን ክህሎት ለማሳደግ በሚረዱ ሥልጠናዎች ውጤታማ ሥራ ማከናወኑን አንስተው፤ የኢፕድን የሥልጠና አቅም በመጠቀም ተቋማት ሰፊ ሥራ ማከናወን እንደሚችሉ ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል።

በዚህ ረገድ በቀጣይ ለሚከናወኑ ሥልጠናዎች የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል ብለዋል።

ሁሉም የኮሙኒኬሽን ባለሙያጋ መድረስ ያለበት ሥልጠና በመሆኑ ተቋማትና የኮሙኒኬሽን አመራሮች በቀጣይ ለሚከናወኑ ተመሳሳይ ሥልጠናዎች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሥልጠናው በተሟላ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ላደረጉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አመራሮችና ባለሙያዎች ሚኒስትር ዴኤታው ምስጋና አቅርበዋል።

በሥልጠናው ማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ፣ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) እና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ ተገኝተዋል።

ኢፕድ ባዘጋጀው ሥልጠና የመደመር ዕሳቤ፣ አዲሱ ፓራዳይምና የኢትዮጵያ ብልጽግና ጉዞ፤ የሕዝብ ግንኙነት መሠረቶች፤ አጀንዳ ቀረጻና የቀውስ ጊዜ ኮሙኒኬሽን፤ ሚዲያ ማኔጅመንትና የንግግር ዝግጅት እንዲሁም የማኅበራዊ ሚዲያ ደህንነትና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሥልጠና ጽሑፎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

«ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና» በተሰኘው የሥልጠና መርሃ ግብር ላይ የቀረቡ ጽሑፎችና የውይይት ሃሳቦች የኮሙኒኬሽን ሙያተኛውን አቅም በመገንባት ረገድ ላቅ ያለ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን ሠልጣኞቹ ተናግረዋል።

በሥልጠናው ማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ እና የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም ተገኝተዋል።

# ለአገርና ለሕዝብ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለጎን ሁሉም ወገን የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል።

«የመደመር ትውልድን መቅረጽ» የሚቻለው ዕውቀት ያለው፣ በውይይት የሚያምን፤ ሥነ ምግባርን የተላበሰና በቂ ክህሎት የጨበጠ ማድረግ ሲቻል ነው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሀኑ፤ ለዚህ ደግሞ ቤተሰብ፣ የትምህርት ተቋማትና የአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ገልጸዋል።

ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም የሚያሰፍን፣ የተፈጥሮ ሀብቷን የሚጠቀምና ኢኮኖሚዋ የዳበረ አገር ለማድረግ በትጋት የሚሠራ ትውልድ ለመቅረጽ ብዙ መሥራት እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ ለአገርና ለሕዝቡ የሚሠራ ትውልድ ለመቅረጽ ትምህርት ቤቶች ከንድፈ ሀሳብ ትምህርት ጎን ለጎን የተግባር ትምህርት ለመስጠት እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ጠቅሰዋል።

በትምህርት ዘርፉ ውጤት የሚያመጡ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ገልጸው፤ በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሌብነትን ለማስቀረት በተሠራው ሥራም የትምህርት ጥራቱ ውድቀት ያለበትን ደረጃ ማወቅ መቻሉን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት 47ሺህ ትምህርት ቤቶችም የትምህርት ሚኒስቴርን መስፈርት የሚያሟሉ ስድስት ትምህርት ቤቶች ብቻ መሆናቸውን ገልጸው፤ የእነዚህ ትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻልም በአገር አቀፍ ደረጃ ሁሉም የሚሳተፍበት ዘመቻ የሚጀመር መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሚኒስቴሩ የትምህርት ሥርዓትን ከማሻሻል ጀምሮ በርካታ የሪፎርም ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመው፤ ከነዚህ ሥራዎችም መካከል ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ እንዲሆኑ የሚያስችል አሠራር መዘርጋቱ፣ በትምህርት ጥራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራቱ እና የትምህርት ቤቶችን ደረጃዎች ለማሻሻል ታቅዶ መሥራቱ እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል። እነዚህም ሥነ ምግባር የተላበሰ፣ የሥራ ባህሉ ጠንካራና በምክንያት የሚያምን ትውልድ ለመገንባትም ትልቅ ሚና ያላቸው መሆኑን አብራርተዋል።

ወዴት እንደሚሄድ የሚያውቅና ችግሮችን እየፈታ የሚያልፍ ትውልድ ለመገንባት አሁንም ብዙ ሥራ ይጠይቃል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ በተለይ በትምህርት ትውልድን ለመቅረጽ ቤተሰብ፣ የማህበረሰብ ተቋማት እና ትምህርት ቤቶች የእውቀት ፍላጎትን በመፍጠር፣ ክህሎትን በማዳበር እና አብሮ መኖር እንዴት እንደሚቻል በማስተማር ሠላማዊ ትውልድ መፍጠር ሁሉም ኃላፊነት ያለበት መሆኑንም አስገንዝበዋል።

የለባዊ ዓለም አቀፍ አካዳሚ ሥራ አስኪያጅ ፕሮፌሰር ፓኖስ ሀዘንድሪያስ በበኩላቸው፣ በትምህርት ሥርዓታችን ተማሪዎች ውስጣቸው ያሉትን ክህሎት በማውጣት እራሳቸውን መሆን እንዲችሉ የሰዋዊ ክህሎታቸውንና የአገር በቀል እውቀትን ማሳደግ ላይ ማተኮር ይገባል ነው ያሉት።

በተለይ ተማሪዎች የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታን የተረዱና ዓለም አቀፋዊነትን የተላበሱ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ዕውቀቶችንና ክህሎቶችን ለማስጨበጥ የትምህርት ሥርዓቱ ይህን ታሳቢ ማድረግ እንዳለበት አመልክተው፤ አዲሱን ትውልድ መልካም ስብዕና የተላበሰ አድርጎ ለመቅረጽ በሁሉም መስኮች እኛ የአርአያነት ሚና መጫወት ይጠበቅብናል ብለዋል።

አዲሱን የመደመር ትውልድ ለመቅረጽ በሚደረገው እንቅስቃሴ አሁን አገራችን ያለችበትን አውድ በመረዳት የአሁኑ ትውልድ የገባበትን ውስብስብ ችግር በመፍታት ቤተሰብና የትምህርት ተቋማት ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚያስፈልግ የገለጹት የሥነ ልቦና ባለሙያዋ ሰብለ ኃይሉ በበኩላቸው፤ በመጀመሪያ በአዲሱ ትውልድ ያለውን የአመለካከት መራራቅ ማቀራረብና ጽንፍ የወጡ አስተሳሰቦችን ማረቅ ላይም አተኩሮ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

የመደመር ትውልድን ለመቅረጽ የትምህርት ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የመምህራን አቅምና ሥነምግባር ማሻሻል፣ የትውልዱን የንባብ ባህል ማሳደግ እና የምን አገባኝ ስሜትን ማስወገድ ይገባል የሚሉ ሃሳቦችም በውይይቱ ተሳታፊዎች ተነስተዋል።

# «የልዩ ኃይል ሪፎርም የሚካሄደው የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያረጋግጥ፣ የአገርን አንድነት የሚያጸና ጠንካራ የጸጥታ ኃይል ለመገንባት ነው»

**- አቶ ግርማ የሺጥላ**
**የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባሕር ዳር፡- የአማራ ልዩ ኃይል መከላከያ ሠራዊት በተከዳበትና አገር ኅልውናዋ አደጋ ውስጥ በገባበት ወቅት መስዋእትነት የከፈለ መሆኑን የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ አስታወቁ።

አቶ ግርማ ከአሚኮ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት የልዩ ኃይል ሪፎርም የሚካሄደው የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያረጋግጥ፣ የአገርን አንድነት የሚያጸና ጠንካራ የጸጥታ ኃይል ለመገንባት ነው።

የልዩ ኃይል ሪፎርምን ተከትሎ በአማራ ክልል የተፈጠሩ አለመግባባቶች ምክንያታቸው ጉዳዩን በሚመለከት የግንዛቤ ሥራ በአግባቡ ባለመሠራቱ ነው ብለዋል።

የክልል ልዩ ኃይሎችን ሪፎርም የማድረጉ ጉዳይ የቆየ ውሳኔ ነው ያሉት አቶ ግርማ፤ በሰሜኑ ግጭት ምክንያት ተግባሩ መዘግየቱን አብራርተዋል።

በክልሉ መከላከያ ሠራዊት ሲንቀሳቀስ ሌላ ኃይል እንደገባ ተደርጎ የሚሠራጨው አጀንዳ አንድ ጠንካራና ወጥ መከላከያ ለመገንባት የሚደረገውን ሂደት የሚጎዳ እንደሆነም ገልጸዋል። ወደ አማራ ክልል ምንም ዓይነት የተለየ ኃይል እንዳልገባም አረጋግጠዋል።

የአማራ ሕዝብ የደረሰበትን መፈናቀል፣ ሞት እና አለመረጋጋት የክልሉ መንግሥትና ብልጽግና ፓርቲ በልዩ ትኩረት ችግሩን ለመፍታት እየሠሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

በተለይም ከክልሉ መሪዎች እውቅና ውጪ ከልዩ ኃይል ሪፎርም ጋር በተያያዘ በማኅበራዊ ሚዲያ ልዩ ኃይሉ ትጥቅ እንደሚፈታ ተደርጎ የተሠራጨው መረጃ ትክክል አለመሆኑን አስገንዝበዋል።

በሪፎረሙ ትጥቅ ስለመፍታት የተላለፈ ውሳኔ እንደሌለም አረጋግጠዋል። በቀጣይም በሰከነ መንገድ በጉዳዩ ላይ በመወያየት የመልሶ ማደራጀት ተግባሩ እንደሚከናወን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ እንደአገር አስተማማኝ ሰላም ያስፈልጋታል ያሉት አቶ ግርማ ይህንን ለማሳካትም የአማራ ክልል በትልቅ ኃላፊነት እየሠራ ነው ብለዋል።

«የአማራ ልዩ ኃይል በክልሉ ሕዝብና መንግሥት ትልቅ ዋጋ ተከፍሎበታል፤ ይህ ኃይልም ፖለቲካዊ ትርጉሙ ከፍ ያለ ነው» ብለዋል። ይልቁንስ የአገርና የሕዝብ አለኝታነቱን ይበልጥ የሚያሳይበትን አደረጃጀት ተከትሎ እንዲደራጅ ይደረጋል ነው ያሉት።

የአማራ ክልል በጦርነት ውስጥ የቆየ ነው፤ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እየተከናወኑ በመሆኑ እነዚህ ተስፋ ሰጪ ሥራዎችም መሰናከል የለባቸውም ብለዋል።

መንግሥት ሁሉንም ነገር በውይይት ለመፍታት ዝግጁ መሆኑን ያስታወቁት አቶ ግርማ፤ በዚህ ወቅት በመደማመጥ ችግሮችን በመፍታት ለአማራ ሕዝብ የሚያስፈልገው ሰላም መሆኑን አስገንዝበዋል ሲል የዘገበው አሚኮ ነው።

# ኢትዮጵያን ማስቀጠል ያስቻሉ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መልካም የሆኑ እሴቶቻችንን በመፈለግና በመሰብሰብ ልናጠናክራቸው ይገባል ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ እሴቶቻችን ለአገር አንድነት ትልቅ መሠረት የሚጥሉ በመሆናቸው ሀሳብ በማዋጣት የአገር ምሰሶና ካስማ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተመራማሪና የሶሾሎጂ መምህር ዶክተር ዘላለም ተፈራ፤ በባህል እሴቶቻችን ላይ እየገጠሙ ያሉ ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ የውይይት መነሻ ጥናት አቅርበዋል።

ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ በጎና በጎ ያልሆኑ እሴቶችን በመለየት በተገቢው መንገድ ልንይዛቸው ይገባል። ማህበራዊ እሴቶቻችንን ከባህላዊና ኃይማኖታዊ ሥርዓቶቻችን በማዋሀድ በአግባቡ መያዝ ያስፈልጋል። ለውጦች መጡ፣ ባህሎቻችን ተሸረሸሩ ከማለት ይልቅ እንዴት እንመልሳቸው ብሎ አስቦ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን ለኃማኖታቸው ቀናኢ፣ ምግባረ ሰናይና ደጋግ ሕዝቦች መሆናቸውን በጥናታቸው ያመላከቱት ዶክተር ዘላለም፤ ሕይወት በትውልድ ይቀጥላል፤ ትውልድ ደግሞ በእሴት ይቀረጻል። ስለሆነም የጋራ እሴቶቻችን በጋራ እንዳቆዩን ሁሉ አሁንም ለመጪው ትውልድ የሚተላለፉ እሴቶችን አጥብቆ መኖር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት አብሮነታችን እንዲቀጥል ያደረጉት በጎ እሴቶቻችን እየተሸፈኑ መጥተዋል ያሉት መምህሩ፤ ዛሬ ላይ ምን ጐደለ፣ ደግነት፣ እርስ በእርስ መከባበር በምን ደረጃ ላይ ነው የሚሉትን መፈተሽና መመለስ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያን ያኖራት መልካም ጉርብትና ነው፤ እውነትን መፈለግና ሀሰትን መኮንን ነው ሲሉ በመነሻ ጽሑፋቸው አመላክተዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነጽሑፍና የፎክሎር መምህር መሐመድ ዓሊ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ እሴት ሲባል ሰዎች የሚፈልጉትንና የሚበጃቸው ነገር መሠረት አድርገው የሚያወጧቸው ሕጎችና ደንቦች ናቸው። እሴቶች ብዙ ጊዜ የመቆየት ባህል አላቸው። ስለሆነም መልካም እሴቶችን በማጉላት አንድነትን ማጠናከር ላይ መሥራት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያን ያኖራት ማህበራዊ ኑሮና መልካም ጉርብትና መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር መሐመድ፤ መከባበር፤ እንግዳ ተቀባይነት፣ አርበኝነት የኢትዮጵያውያን እሴቶች ነበሩ። አሁን የት ገቡ፣ የጎደሉና የተሸረሸሩ ጉዳዮችን ብሎ ለይቶ ማከም ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃን አገራዊ እሴቶችን የሚያጎሉ የፎክሎር ሥራዎችን ወደ ፊት በማምጣት ማህበረሰቡ ነባር ባህሉ እንዲዳብር ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ይልቅ ዘላቂ ሰላምን ማስቀደም ይቅደም!

ፖለቲካ በጥበብ የመምራት ችሎታን ይጠይቃል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝብና ሀገርን ማስቀደም፣ልዩነትን ማቻቻል፣ ለሰላምና ለዴሞክራሲ መቆምን ይሻል፡፡ ከራስ ፍላጎትና ምኞት ይልቅ ለህዝብና ለሀገር ፍቅርና ተቆርቋሪነትንም ያስቀድማል፡፡ እንደ ስልጡን ማህበረሰብ መመካከርና መወያየትም አብዝቶ ይፈልጋል፡፡

የሀገራችንን የትናንትም ሆነ የዛሬ የፖለቲካ ታሪክ ስንመለከተው ደግሞ፣ እውነታዎች የተገላቢጦሽ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ አንዳንድ ፖለቲከኞች ከመወያየትና ከመመካከር ይልቅ መዝለፍ የሚቀናቸው፣ ከዘላቂ የሀገር ሰላምና ዕድገት ይልቅ ጊዜያዊ ጥቅም የሚበረታባቸው፣ ስልጣንን በምርጫ አሸንፎ ከመረከብ ይልቅ የተለያዩ አጀንዳዎችን እና ውዥንብሮችን በመፍጠር በአቋራጭ ለመቆናጠጥ የሚሞክሩ፣ ለዚህም ሌት ተቀን የሚተጉ ናቸው።

ሰበብ እየፈጠሩ የህዝብን ስሜት መቀስቀስና ሰላም እንዲደፈርስ ማድረግን እንደ አንድ የፖለቲካ ግብ አድርገው የሚወስዱ፣ ለዚህም የተሳሳቱ መረጃዎችን በስፋት ወደ ሕዝብ ጆሮ ከመልቀቅ ጀምሮ የጥፋት ትርክቶችን በመፍጠር ሕዝብን ከመንግስት ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማጋጨት ያዘወትራሉ፣ ከሚፈጠረው ግጭትም አትራፊ ለመሆን ያለመታከት የሚሰሩ ናቸው።

እነዚህ የፖለቲካ ሀይሎች / ተዋናዮች ከያዙት የፖለቲካ ስትራቴጂ አንጻር ያልተረዷቸው ሁለት መሰረታዊ ነገሮች አሉ ፡፡ አንደኛው ስልጣን ላይ ወጥቶ ሀገር መምራት የሚቻለው ሰላም ሲኖር ብቻ እንደሆነ፣ ሁለተኛው ደግሞ ለስልጣን መሻታቸው ብለው የሚጠምቁት ጥፋት ለነሱም የሚተርፍ የከፋ መንገድ መሆኑን ነው።

ሰላም በሌለበት እንኳንስ ሀገር መምራት በህይወት የመቆየት ዋስትናን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሸክሟ በከበደ ሀገር ላይ በፖለቲካ ውስጥ ያሉ ተዋናዮች እሩቅ አሳቢ ካልሆኑ በቀር ፣ የስልጣን መሻታቸውን ብቻ እየተከተሉ በጭፍን የሚሄዱበት መንገድ ሀገርና ህዝብን ሊያስከፍል የሚችለው ያልተገባ ዋጋ የከፋ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ምክንያቱም ኢትዮጵያ ዘመንና ትውልዶችን የተሻገሩ በርካታ ችግሮች የተጋረጡባት ሀገር ነች፡፡ ለሀገሪቱና ለህዝቦቿ እናስባለን የሚሉ ፖለቲከኞች የችግሮቹን ስፋትና ጥልቀት በሚገባ ተረድተው በብዙ ማስተዋል መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ የሚሆንም የፖለቲካ ስብእና ሊገነቡ ያስፈልጋል።

የቀደሙት ችግሮቻችን ትተን አሁነኞቹን እንኳን ብናስብ፣ ለሁለት አመታት ያህል በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተካሄደው ጦርነት የፈጠረብን ሀገራዊ ቁስል ገና አላገገመም፡፡ ድርቅ ዛሬም እየተፈታተነን ነው፣ መልከ ብዙ የኑሮ ውድነት የህዝባችን ዋነኛ ፈተና ከሆነ ውሎ አድሯል። ስራ አጥነት ገና ያልተፈታ ችግር ነው፣ የዕዳ ጫና እና የውጭ ሀገራት ፖለቲካዊ ተጽዕኖም ገና ፈር ያልያዘ ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህና መሰል ችግሮች ባልተፈቱበት ሀገራዊ አውድ ሌሎች ተጨማሪ ችግሮችን እየቀመሩ የፖለቲካ ገበያውን የግጭትና የሁከት ገበያ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት በግልጽ ከሀገርና ህዝብ ጥቅም በተቃራኒ ከመቆም የተለየ አይደለም፣ የህዝባችንንም የዴሞክራሲ ስርአት ተገንብቶ የማየት መሻት በአደባባይ የመጻረር እኩይ ተልእኮ አካል ነው።

በአሁኑ ሰአት መርህ አልባ በሆነ መንገድ፣ ሀገርና ህዝብን አደጋ ውስጥ በሚከት የጥፋት ተልእኮ ውስጥ የምትገኙ የፖለቲካ ሀይሎች / ተዋናዮች ከዚህ ተግባራችሁ ልትታቀቡ ይገባል፡፡ ይህ ተግባራችሁ ነገ ከነገ በስቲያ የሞራልም፣ የህግም ተጠያቂነትን ሊያስከትል እንደሚችል ማሰብ ተገቢ ነው።

መንግስት ለጀመረው የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስኬት የፈጠረውን ሆደ ሰፊነት ፣ በአግባቡ ተገንዝቦ መመላለስ፣ ለሀገርና ለህዝብ ዘላቂ ጥቅም ሰከን ማለት ከእናንተ ይጠበቃል፡፡ በተለይ በዚህ ጊዜ በሰከነ መንገድ መነጋገርና መደማመጥ ወሳኝ ነው፡፡ ሰሞኑን ልዩ ኃይሎችን መልሶ ከማደራጀት ጋር በተያያዘ የሚስተዋለውን ጉዳይም በዚሁ ልክ መገንዘብም፣ ማየትም ያስፈልጋል፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለጸው እና በህገ መንግስቱም ላይ በማያሻማ መልኩ እንደተመለከተው፣ ሀገርን እና ህዝብን ከየትኛውም ጥቃት እና ጠላት የሚከላከል ሀገራዊ ሀይል የመገንባት ኃላፊነት እና ስልጣን የፌዴራል መንግስቱ ብቻ ነው፡፡ የክልል መንግስታትም የክልላቸውን ሰላምና ጸጥታ የሚያስጠብቅ ክልላዊ ፖሊስ አደራጅተው እንደሚመሩ በህገ መንግስቱ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህም ይህንን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ውይይትና ምክክርን መሰረት ባደረገ መልኩ ወደ መሬት ማውረድ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያም በበርካታ ችግሮች ትከሻዋ የዛለ ሀገር እንደመሆኗ፣ ተጨማሪ ችግሮችን እንድታስተናግድ መንገድ ማበጀት አይገባም፡፡ ከዚህ የተነሳ በፖለቲካው ውስጥ ካሉ ተዋናዮች ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ በአግባቡ መረዳት እና በኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ፣ ከጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ይልቅ ዘላቂ መፍትሄ ማፈላለግና ሰላም ማስፈን ላይ ማተኮር ይጠበቃል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአገር ሉዓላዊነትን፣ የሕዝቦችንም ሰላምና ደህንነት በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ

ዳንኤል ዘነበ

ላለፉት አስርት ዓመታት በሀገሪቱ የሚገኙ ክልሎች የራሳቸውን ልዩ ኃይል ሲያደራጁና ሲያስታጥቁ ቆይተዋል። ይህንንም ተከትሎ ተግባሩ በዜጎች ዘንድ የተለያዩ ትርጓሜዎች ሲሰጠው ቆይቷል፡፡ አንዳንዶች ልዩ ኃይሉ የአንድን ክልል ሕዝብ ደህንነት ለማስጠበቅ ከፖሊስ ባሻገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ሲሞግቱ ፣አብዛኞች ግን ከፍያሉ የደህንነት ስጋቶችን የመመለስ ስራ የመከላከያ ሰራዊት ነው በሚል አደረጃጀቱን ሲሞግቱ ቆይተዋል።

ለዚህ ሃሳባቸው ማጎልበቻም አደረጃጀቱ ህገ መንግስታዊ መሰረት የሌለው ፣የሚያካሂዳቸው ተግባራት በሙሉ ሕጋዊ መሰረት የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ፣ ችግሩ ከህጋዊነት ባለፈም ለአገር ደህንነት ስጋት ሊሆኑ የሚችልበት እድል ከፍ ያለ መሆኑን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲጮሁ ተደምጠዋል፡፡

በተለይም ባለፉት አምስት አመታት /ከለውጡ ማግስት ጀምሮ/ የልዩ ኃይል ጉዳይ በተለያየ መልኩ ጎራ ፈጥሮ ሲያከራክርና ሲያጨቃጭቅ ቆይቷል። በእርግጥም እኔን ጨምሮ ብዙዎች የክልል ልዩ ኃይሎችን "መፍረስ" አለበት የሚል አቋም ይዘን እንደነበር የአደባባይ ሚስጥር ነው ። ዛሬ ላይ የልዩ ሀይሉን ዳግም በአዲስ መልክ በህጋዊ መልኩ መደራጀቱን የሚቃወሙ ሳይቀሩ "ልዩ ሀይል ይፍረስ" እያሉ ሲጮሁ እንደነበር ብዙ ብዙ ምስክር መጥቀስ የሚያስፈልገው እውነታ አይደለም።

በርግጥ የክልል ልዩ ሃይሎች የተደራጁበት ስነ ልቦና ያላቸው ቁመና ፣ ክልል ከክልል የነበራቸው ፉክክር በአገራዊ አንድነት ላይ ትልቅ ስጋት ሆነው እንዲታዩ እንዳደረጋቸው የሚካድ አይደለም።

ከዚህም ባለፈ አንዳንድ ክልሎች በልዩ ሀይል ስም ያደራጇቸው ሀይሎች ከአንዴም ሁለት ጊዜ የሀገርን ሕልውና አደጋው ውስጥ ከትተው እንደነበር ይታወሳል። ችግሩን ለመቀልበስ የተከፈለው ዋጋም የቱን ያህል ከፍ ያለ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ጠባሳውም ገና አላገገመም።

በአንዳንድ ክልሎች እነዚህ ሀይሎች የክልሉን መንግስት ከማገልገል ወጥተው ለግለሰቦች ፍላጎት ተገዝተው ሲንቀሳቀሱ ታዝበናል። አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው አገርን ወደ ዘመነ መሳፍንት የመመለስ ስጋት ይዞ እንደነበር በተጨባጭ አይተናል።

በርግጥ መንግስት በግልጽ ለማሳየት እንደሞከረው፣ የክልሎች ልዩ ኃይሎች በሙሉ የክልላቸውን ፀጥታ ይጠብቁ ነበር፣ ከመከላከያ ሀይሉ ጋር አብረው ቆስለዋል፣ ደምተዋል፣ ሞተዋል። ይህ ኃይል ይህንን የመሰለ ትልቅ ማንነት አለው። ይህንን በሙሉ ያከናወነው መከላከያው እያስተባበረውና እየመራው።

ከህገ መንግስት አንፃር ስናይ እነዚህ ኃይሎች ህጋዊ አይደሉም። ህገመንግስቱ እውቅና አይሰጣቸውም። ለክልል ኃይል የሚሰጠው መደበኛ ፖሊስን ብቻ ነው። ህገመንግስቱ የታጠቀን ኃይል የሚሰጠው አንደኛ መከላከያን፣ ሁለተኛ ፌዴራል ፖሊስ፣ ሶስተኛ ደግሞ የክልል መደበኛ ፖሊስ ነው። ከዚህ ውጭ ህገመንግስቱ መብት የሚሰጠው ታጣቂ ሀይል የለም። ከዚህ የተነሳ ይሄ ኃይል ህጋዊ አይደለም። ስለዚህ ህጋዊ መስመር መያዝ አለበት። ወደ ህጋዊ መስመር እንዲገባ መደረግ ይኖርበታል።

ሌላው ችግር የሀይሉ አገነባብ ብሄር ተኮር መሆኑ ነው። ብሔር ተኮር ሲባል ኦሮሞው «ለኦሮሞ ህዝብ እሞታለሁ» የሚል፣ የሶማሌው፣ የአፋሩ፣ የአማራው፣ የሲዳማው፣... በተመሳሳይ የሚልበት አካሄድን የሚፈጥር ነው፡፡ ይህ ማለት የሌላው ብሄር ጉዳይ ጉዳዬ አይደለም የሚል መንፈስን ስለሚላበስ ሂደቱ የህዝቦችን አንድነት የሚሸረሽር ነው።

ከዚህም በላይ አዘገጃጀቱ የአገሪቷን የፖለቲካ መፍቻ መንገድ አበላሽቷል።በየትኛውም አገር፣ በእኛም አገር ህገመንግስት ፖለቲካና ጉልበት አብሮ አይሄድም። በእኛ አገር ፖለቲካና ጉልበት የሰጠው ህገመንግስቱ በህዝብ ለተመረጠ መንግስት ብቻ ነው። ስለዚህ የክልል ልዩ ኃይል ፖለቲከኛው በሃሳብ ማሸነፍ ሲያቅተው ለሌላ በትር እድል ሰጥቷታል። ሁለት ዓመት ሙሉ በጦርነት የቆየነው በዚህ ምክንያት ነው።

ይህ ሀይል ከዚህ በከፋ መልኩም ለአገርና ለሁሉም ህዝቦች የሚሞተውን መከላከያ ሰራዊት መገዳደር የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ደግሞ ከሀገርና ከህዝቦች ሰላምና ደህንነት አንጻር ምን ማለት እንደሆነ ለመገመት አይከብድም።

ከዚህ አኳያ ቀደም ሲል ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችንም ሆነ መንግስት በጥናት የደረሰባቸውን ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት የክልል ልዩ ኃይሎችን ወደ ፌዴራልና የክልል ህጋዊ የፀጥታ መዋቅር ውስጥ ገብተው የአገር መከላከያን ማጠናከር አለባቸው የሚለው የመንግስት ውሳኔ ተገቢነት ያለው እንደሆነ አምናለሁ።

የለውጡ መንግስት እንደመጣ የመጀመሪያው እርምጃ ይህ ይሆናል ብዬ ጠብቄ ነበር። ይሁን እንጂ ባለፉት አምስት የለውጥ ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች አደረጃጀቱ እንደነበረ ሊቀጥል ችሏል። ነገር ግን ዘግይቶም ቢሆንም አሁን መንግስት የአብዛኛው ህዝብ ጥያቄ ለሆነው ለዚህ ሀገራት ችግር መፍትሄ ለመስጠት እንቅስቃሴ መጀመሩ የሚያስመሰግነው ነው። ውሳኔው የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መጠበቅ የሚያስችል አንድ ጠንካራ የተማከለ ሠራዊት መገንባት የሚያስችል ጥልቅ እርምጃ ይመስለኛል።

የመንግስት ውሳኔ ትልቅና ኃላፊነት የተሞላበት፣ ከልዩ ሀይሉ ጋር ሲነሱ የነበሩና አሁንም የሚነሱ ተገቢ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል ከመሆኑም ባለፈ፡፡ በእነዚህ አደረጃጀቶች ውስጥ የነበረው የሰው ኃይል የተሻለ ሀገራዊ ኃላፊነት ወስዶ ውጤታማ የሚያደርገውን አቅም የሚያላብሰው ነው። በዚህም አገራዊ እፎይታን እንጂ ስጋት ሊፈጥር የሚችል አይደለም።

በአገራችን ሲፈጠሩ ከነበሩ ችግሮችና ካሳለፍናቸው አስቸጋሪ ጊዜያት አኳያ ፣ የመንግስት ውሳኔ በመዘግየቱ ሊያነጋግር ከመቻሉ ባለፈ ተግባራዊ በመሆኑ ማንንም ሊጎዳና ስጋት ውስጥ ሊጨምር የሚችል አይደለም።እዚህ ላይ በአግባቡ ሊታይ የሚገባው የየትኛውም ኢትዮጵያዊ ሰላምና ደህንነት ዋንኛ አቅም/መተማመኛ የሀገሪቱ የመከላከያ ሀይል መሆኑ ነው።

እዚህ ላይ በግልጽ መታወቅ ያለበት አሁን ላይ የመንግስት ውሳኔ በመቃወም ላይ የሚገኙ ሀይሎች ፣የአገር ሉአላዊነት ጉዳያቸው ያልሆኑ አክራሪ ብሔርተኞች እና ጽንፈኞች ናቸው፣ ካልሆነም እነዚሁ ኃይሎች ባልተገባ መንገድ ግፍ ያደረሱባቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ ጩኸታቸውም ግብ ያደረገው የሀገሪቱን የመከላከያ እና የጸጥታ ሀይሎች አቅም በመገንባት ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የሚደረገውን ሀገራዊ ጥረት ለማደናቀፍ ነው።

በአጠቃላይ የክልል ልዩ ሀይሎችን በአዲስ መልክ ለማደራጀት በመንግስት በኩል የተደረሰበትን ውሳኔ ተከትሎ የሚናፈሱ አሉባልታዎች የጥፋት ሀይሎች አጀንዳ መሆኑን ዜጎች ተገንዝበው፣ ለነዚህ ሀይሎች ጆሮ መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡ መንግስትም ስራውን በጀመረው መንገድ ከህዝብ ጋር በመወያየት ሰላማዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ህዝብም የውሳኔውን ፋይዳ ከግምት በማስገባት ለውጤታማ ትግበራው ተገቢውን ትብብር ሊያደርግ ይገባል፡፡

# ተጠየቅ

# ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ችግር በ2017 ዓ.ም ዘላቂ መፍትሔ ያገኛል››

- ዶክተር ገበየው ሊካሳ
የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ



ክብረአብ በላቸው

**በሀገሪቱ የመልካም አስተዳደር ችግር ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተለይም በብዙ ተቋማት የሚሰጠው አገልግሎት ችግር የሚታይበት በመሆኑ ይህ የመልካም አስተዳደር ችግር ዜጎችን ሲፈትን ይስተዋላል፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ መሆኑ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ለዚህ ችግር መፍትሔ ቢሆን በሚል በተለያየ ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ለማነጋገር ተሞክሯል፡፡ ዛሬም ድረስ ግን ችግሩ አልተቀረፈም፡፡ ችግሩ ደግሞ በአዲስ አበባ በስፋት ይስተዋላል፡፡ ይህ ለምን ሆነ? ዘላቂ መፍትሔው ምንድነው? በሚል አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ገበየው ሊካሳ ጋር ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በተገልጋይ እርካታ ያለፉት ወራት አፈፃፀም ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ገበየው፡-** የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ዘመናዊ ለማድረግና የኅብረተሰቡንም እርካታ ያረጋገጠ እንዲሆን ብዙ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም ተቋሙ ብዙ ተግዳሮቶች የነበሩበት ነው፡፡ ከ2002 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ከፍተኛ የግብዓት እጥረት የነበረበት ከመሆኑ በተጨማሪ የቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ላይም ዘገምተኛ በመሆኑ የደንበኞች ቅሬታ ምንጭ ሆኖ ከርሟል፡፡ ይህንን ለመለወጥ ባለፉት አራት እና አምስት ዓመታት በተለይ የኃይል መቆራረጥና የገንዘብ አሰባሰብ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ለአብነት ያህል የኃይል መቆራረጥን ከመቀነስ አኳያ የስትራቴጂክ እቅድ ተቀርፆ በአራት ምዕራፍ አዲስ አበባ ውስጥ የማከፋፈያ መስመሮች ላይ የመልሶ ግንባታ ሥራ ተከናውኗል፡፡

ሁለቱ ምዕራፍ እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ተጠናቋል፡፡ ይህም 10 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያለው ፕሮጀክት ነው፡፡ እነዚህ ተጠናቀው ወደ አገልግሎት ሲገቡ የደንበኞች ቅሬታ እየቀነሰ፣ የኃይል መቆራረጡም እየተሻሻለ ይመጣል፡፡ በሌላ በኩል የክፍያ አማራጮችን ከማስፋት አኳያ ቴክኖሎጂን ስለተጠቀምን ደንበኛ በደረሰበት ቦታ መክፈል ይችላል። ከዚህ ቀደም ከአንደኛው የሀገሪቱ ክፍል ሆኖ በባንክ ክፍያ መፈጸም የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን ይህ ተችሏል፡፡ በእርግጥ በታሰበው ልክ ባይሆንም የደንበኞች እርካታ ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

እኛ የደንበኞችን እርካታ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በየስድስት ወሩ ግምገማ እናካሂዳለን፡፡ በዓመት አንዴ ደግሞ በውጭ አካል ከዓለም ባንክ ጋር በመሆን እናሠራለን፡፡ ለምሳሌ የዘንድሮውን ለአብነት መጥቀስ ካስፈለገ በሦስተኛ ወገን ባስጠናነው ጥናት ተቋሙ አፈፃፀሙ 61 በመቶ ላይ ነው፡፡ አምና 58 ከመቶ ነበርን፤ አሁን ሦስተኛው ምዕራፍ ፕሮጀክት ደግሞ እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ግማሽ ላይ ይጠናቀቃል፡፡ ይህ ሲጠናቀቅ የኃይል መቆራረጡ ይቀንሳል፡፡ ከዚህም የተነሳ የደንበኞች እርካታ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱ ያሳችሁበትን ደረጃ አመላክቷችኋል ?**

**ዶክተር ገበየው፡-** በእኛም ሆነ በውጭ የተጠናው ጥናት ብዙ እንደሚቀረን አመላክቶናል፡፡ ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅብንም አስተውለናል፡፡ ከለየናቸው ክፍተቶች አንደኛው አስቀድሜ የጠቀስኩት የኃይል መቆራረጥ ነው፡፡ ሌላው ከ2002 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ከፍተኛ የሆነ የግብዓት እጥረት ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት ከፍለው የሚጠባበቁ ብዙ ደንበኞች ነበሩ፤ አሁን ግን እየጨረስን ነው፡፡ እነዚህን በሙሉ እያጠናቀቅን ስንመጣ የደንበኞቻችን እርካታ ይሻሻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በግምገማችሁ በዋናነት ችግር ነው ብላችሁ የለያችሁት ዘርፍ የትኛው ነው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** እንደጠቀስኩት አንዱ የቅሬታ ምንጭ የኃይል መቆራረጥ ነው፡፡ ይህን መሠረታዊ በሆነ ደረጃ ለመፍታት አስቀድሜ እንደጠቀስኩት በአራት ምዕራፍ የተከፋፈለ የሪሃቢሊቴሽን (Rehabilitation) ፕሮጀክት አለ፡፡ ነባራዊ ሁኔታው ሲታይ ኔትወርኩ በጣም ያረጀ ነው፡፡ ይህን ለመቀየር ስትራቴጂክ ዕቅድ ተነድፎ እየተሠራ ነው፡፡ የሁለቱ ምዕራፍ ፕሮጀክት ተጠናቋል፡፡ ሦስተኛው ምዕራፍ በ2016 በጀት ዓመት አጋማሽ ላይ ይጠናቀቃል፡፡ አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ አሁን ተጀምሯል፡፡

የግዥ አማካሪ ቅጥር እየተካሄደ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በዓለም ባንክ የገንዘብ ወጪ የተሸፈነ ነው። ፕሮጀክቱ በ2017 ዓ.ም ሲጠናቀቅ አሁን የሚታየው የኃይል መቆራረጥ ይቀንሳል፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ ሁለት ሺህ የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮችን አቅም የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡ ያሉን አስር ሺህ ናቸው፤ በዚህ ሂደት ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አሠራርን በመጠቀም በተለያየ መንገድ ይሠሩ የነበሩ በአንድ የቁጥጥር ጣቢያ ውስጥ ይገባሉ። ኃይል ሲቋረጥ በቀላሉ ማወቅ ስለሚቻል በኃይል መቆራረጡ ላይ የሚታይ ለውጥ ይመጣል፡፡ ከወቅታዊ የአየር ሁኔታ ጋር የነበረው የኃይል መቆራረጥን አሁን በምንችለው ደረጃ በቅድመ መከላከል ጥገና እና በመልሶ ግንባታ የምንሠራቸው አሉ፡፡ ነገር ግን በመሠረታዊነት ችግሩን ለመፍታት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ የግድ ይላቸዋል፡፡

ሁለተኛው የገንዘብ አሰባሰብ ላይ ክፍያ በዛብኝ፤ ንባብ በትክክል አይወሰድም፤ የተሳሳተ ቢል ነው፤ የሚሉ ቅሬታዎች አሉ፡፡ ይህን ለመፍታት ብዙ መንገድ ሄደናል፡፡ እኔ ወደዚህ የኃላፊነት ስፍራ የመጣሁት በ2012 ዓ.ም ላይ ነው፡፡ ያኔ የነበረው ትልቁ ቅሬታ ሰልፍ ነው፡፡ አሁን ግን በዓመት በዓል ወቅቶች ከሚያጋጥመው ውጭ አንድም ሰልፍ የለም፡፡ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት የቆጣሪ ንባብ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን አድርገናል። የቆጣሪ አንባቢ ቆጣሪው ያለበት ቤት የግድ መሄድ ይጠበቅበታል፡፡ ስለዚህ ችግሩ እየተቀረፈ ነው፡፡ ሌላው የለየነው ችግር አዲስ ከፍለው የሚጠባበቁ ደንበኞች ጉዳይን ናቸው፤ ከ2002 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ ከፍተኛ የሆነ የአቅርቦት እጥረት ነበር። ይህም የራሱ ምክንያት አለው፡፡ ከውጭ ይገባ የነበረ ሁሉም እቃ አሁን ሀገር ውስጥ ይመረታል፡፡ ስለዚህ ከፍለው ያልተስተናገዱትን ደንበኞች ቁጥር እያቃለልን በመሆኑ የቀሩት ከስድስት ሺህ የማይበልጡ ደንበኞች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ደንበኞች ሂሳብ በጣም እንደሚጋነን የሚጠቅሱ ሲሆን፣ እኛም የተጠቀሙበት ስለመሆኑ ሁኔታውን በግልጽ በማሳየት እናሳምናቸዋለን።

**አዲስ ዘመን፡- የምታሳምኗቸው በምን አግባብ ነው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** ባለፉት ዓመታት ሲከፍሉ የነበረው ከአጠቃቀማቸው አኳያ ሲነጻጸር ትንሽ ብር ነው፡፡ በመሆኑም እኛ በጊዜ ያለማስከፈላችን እንጂ የተጋነነ አለመሆኑን እናሳምናቸዋለን፡፡ ከዚያም በክፍያ ሂደቱ ጫና እንዳይፈጠርባቸው እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ጊዜ እንሰጣቸዋለን፡፡ የቢል ስህተት ካለ ደግሞ ይታረማል፡፡ ድሮ ከታተመ አይታረምም ነበረ፤ አሁን ቢል ላይ ስህተት ካለ በአገልግሎት መስጫ ማዕከል ላይ እርምት ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ይህን ሙሉ በሙሉ ተደራሽ አድርገናል ማለት አንችልም፡፡ አሁንም እየሠራንበት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከቆጣሪ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ያለው ፍትሐዊ አሠራር ምን ይመስላል? አገልግሎቱን በወጥነት አትሰጡም፤ ቆጣሪ ቀድመው ተመዝግበው የሚጠባበቁ እያሉ ከኋላ መጥተው ተጠቃሚ የሚሆኑ ሰዎች አሉ ይባላል፤ ለምን?**

**ዶክተር ገበየው፡-** ይህ የሚፈጠርበት ሁኔታ አለ፤ አልፎ አልፎ አንደኛው ደንበኛ አራት ምሰሶ ይፈልጋል ወይም ትራንስፎርመር ይፈልጋል፡፡ ሌላው ደግሞ ከምሰሶ ብቻ በሽቦ የሚገባለት ሊኖር ይችላል፡፡ አንዳንድ ትራንስፎርመር የሚጠብቅ ሰፈር አለ፤ ግን የከፈለው የዛሬ ዓመት ነው፡፡ ምንም ተጨማሪ ነገር ሳያስፈልገው ቆጣሪ ማግኘት የሚችል ሰው ደግሞ ይመጣል፡፡ ለዚህ መስጠት እየቻልን የደንበኛ ቅሬታ ይፈጥራል በሚል መቆም ስለሌለብን እናስተናግዳለን፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ግለሰቦች አሉ። ከውጭ የሚገባን ምርት በሀገር ውስጥ ለመተካት የሚሠሩ፣ በውጭ ላኪነት የተሠማሩ፣ የውሃ ተቋማት እንዲሁም የጤና ተቋማት በአሠራሩ መሠረት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ ነገር ግን ሲስተም ላይ እናውቃቸዋለን። መቼ እንደተመዘገቡ፣መቼ እንደገባላቸው ለኦዲት በሚያመች ሁኔታ እያየንና እነዚህን ችግሮች በአሠራር እየገመገምን ብሎም እየፈታን እየሄድን ነው፡፡ ተመሳሳይ ምሰሶ ከፍሎ እየተጠባበቀ ለአንዱ ቅድሚያ የሚሰጥበት አሠራር ካለ እርምጃ እንወስዳለን፡፡ ሠራተኞች ይህንን አይነት ችግር ፈጠሩ ማለት የፈጠሩት ችግር የሚታይ ስለሆነ መደበቅ አይችሉም፡፡ የሚያየው ቴክኖሎጂ ነው። ስለዚህ ማንም ምንም አድርጎ መደበቅ አይችልም፡፡ ቢል አይወጣለትም፤ ቆጣሪ አይነበብም፤ ስለሆነም ይያዛል፡፡ ይህ ስህተት የመፈጠሩ አጋጣሚ ጠባብ ነው፡፡

ሌላው ሲሪ ፌዝ ቆጣሪ በቅርብ የጀመርነው አገልግሎት ነው፡፡ ሲንግል ፌዝ አመልካቾች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ስሪ ፌዝ አመልካች እያለ ማለት ነው፤ እና ትላልቅ ኬብሎች የሚጠብቁ ደንበኞች ይቆያሉ ወይም ገዝተው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ሌላው ከውጭ የሚገቡ ኬብሎች አሉ፤ ስለዚህ ማስተናገድ የምንችለውን ደንበኛ ይዘን ቁጭ ብለናል፤ ደንበኞች እኛ ዘንድ ከፍለዋል፤ ነገር ግን ማግኘት አልቻሉም። ይህ አይነቱ ጥያቄ ግን ከአንድ ወር ወይም ከ15 ቀን በኋላ ጥያቄ አይሆንም፡፡ ደንበኞች ደግሞ ገዝተው እንዲያቀርቡ ይደረጋሉ፤ ለዚህ ፍቃደኛ የሆነ ወይም የቻለ ሰው ያመጣና ይስተናገዳል፤ ያላመጣ ደግሞ የኛን አቅርቦት ይጠብቃል፡፡ እንዲያውም ትልቁ ምክንያት ይህ ነው፡፡ ደንበኞች ገዝተው ከቀረቡ ቀድመው ለእኛ የከፈሉት ገንዘብ ይመለስላቸዋል፡፡

ከጋራ የመኖሪያ ቤቶች ጋር ተያይዞ አሁን የሚለጠፈው ቆጣሪ ሌላው መሠረተ ልማት ከኋላ ስላልተሟላ ቅድሚያ ያለውን ዕቃ ለመሥራት ነው እንጂ አገልግሎት አይሰጥም፡፡ አሁን አንደኛው ተለጥፎ ሌላው የሚቀረው በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ የሚሠራው አገልግሎት መስጫ ማዕከል ሳይሆን ኮንትራክተር ነው፡፡ ይህንን ሥራ አዳዲሶቹ ኮንዶሚኒየሞች ጋር ያለው ሁኔታ ይህ ነው፡፡ የጨረስናቸው ደግሞ አሉ፤ ቱሪስት፣ እህል ንግድ፣ ኢምፔሪያል፣ መሪ ሎቄ፣ ቦሌ አያት አንድ እና ሁለት፣ አስኮ እንዲሁም ባሻ ወልዴ ቆጣሪም ሆነ ትራንስፎርመርም ተከላ ሙሉ በሙሉ ጨርሰናል። አንዳንድ ቦታ ደግሞ የተወሰነ ቆጣሪ ተለጥፏል፤ ነገር ግን ትራንስፎርመሩን ስላላስቀመጥን ቅድሚያ አንሰጥም። ከዛ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በአንድ ወር ከአስራ አምስት ሺህ እስከ ሃያ ሺህ ደንበኛ ማገናኘት እንችላለን። ነገር ግን አንድ ቆጣሪ ለማገናኘት አስራ አራት አይነት ዕቃ ይፈልጋል፡፡ አንድ ዕቃ ከመሐል ሲጎድል ሥራው ይቆማል፡፡ እነዚህን እና መሰል ችግሮች ለመፍታት እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ዳር መብራት አገልግሎት ሰጥታችሁ የፍጆታ ገቢ በተገቢው መንገድ ትሰበስባላችሁ?**

**ዶክተር ገበየው፡-** በድምሩ በአራቱም ቅርንጫፍ

# ተጠየቅ

ጽሕፈት ቤቶቻችን ስር የሚተዳደሩ አዲስ አበባ ላይ አንድ ሺህ የሚሆኑ የመንገድ መብራት ቆጣሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ቆጣሪዎች በወቅቱ ቢል አንብበን ለማንኛውም ደንበኛ እንደምናነበው ሂሳብ መሰብሰብ መቻል አለብን፡፡ ይህን ደግሞ የሚከፍለው የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ነው፡፡ የመንገድ መብራት የመብራት ኃይል ንብረት አይደለም፤ የትኛውም ሀገር ላይ የሚያስተዳድረው የከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው። ሌላው ዓለም ላይ እኛም ዘንድ የከተማ አስተዳደሩ የሚያስተዳድረው ክፍል አለ፡፡ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ያለውን እያስተዳደረ ያለው የከተማ አስተዳደሩ መንገዶች ባለስልጣን ነው፡፡ ለዚህ የኃይል ፍጆታ በየወሩ እንደማንኛውም ደንበኛ መክፈል አለበት፡፡ እኛም አንብበን የቆጠረባቸውን መላክ አለብን፡፡

የመንገድ መብራት ላይ የተፈጠረው ችግር በ2012 ዓ.ም ERP SYSTEM ተግባራዊ ሲደረግ ዳታ ከአሮጌው ሲስተም ወደ አዲሱ ሲስተም መሸጋገር ነበረበት። በዚህ መሐል የተንጠባጠቡ ደንበኞች አሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ የመንገድ መብራት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሳይከፍሉ ቆዩ፤ ይህ በመሆኑ ምክንያት ሂሳባቸው ተጠራቀመ፡፡ ያለባቸውን ሂሳብ ባሳወቅናቸው ጊዜ በጀት አጣን አሉ፡፡ 2015 ዓ.ም ላይ እንከፍላለን በሚል ጉዳዩ አደረ፡፡ አሁን 2015 ዓ.ም ላይ ደግሞ ሲመጡ በጀታችን አነሰ አሉ፡፡ እስካሁን ተንከባሎ የመጣ፤ ሰባ ሚሊዮን ብር ዕዳ አለባቸው፡፡ እነርሱ የነበራቸው ደግሞ ሃያ ሚሊዮን ብር ነው፡፡ እርሱን ጥቅምት ላይ ከፍለዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ምን ያህል ዕዳ አለባቸው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** አሁን አርባ ስምንት ሚሊዮን ብር ዕዳ አለባቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ ስምን መሰብሰብ አልቻላችሁም?**

**ዶክተር ገበየው፡-** መጀመሪያ አካባቢ የዳታ ለውጥ ጉዳይ ተፈጠረ፤ እኛ 2014 ዓ.ም ላይ ደግሞ የዳታ migration ሥራ ጨርሰን ሂሳብ ስናሳውቃቸው በዚህ ልክ አልተዘጋጀንም አሉ፡፡ እናንተ ያመጣችሁት የተንከባለለ ሂሳብ ነውና በሚቀጥለው በጀት ዓመት እንከፈል በሚል የቆየ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ተቋማት የመብራት ፍጆታ ክፍያ በወቅቱ አይከፍሉም፤ እናንተም በተገቢው መልኩ አትሰበስቡም፤ ይህ ምን ያህል እውነት ነው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** ይህ እውነት አይደለም፤ እኛ እንዲያውም እየተቸገርን ያለነው በሀገር ውስጥ የመንግሥት ተቋማት ነው፡፡ ይህም የሚስተዋለው ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የጤና ተቋማት ላይ ነው፡፡ ደንበኛ ባይከፍል እንቆርጣለን፤ ቆርጠን በሕግ ከሰን ገንዘብ እናስከፍላለን፤በመንገድ መብራት ላይ ይህን ማድረግ አልቻልንም፡፡ የእኛም ጥፋት አለበት፤ አንዳንድ ተቋማት ደግሞ ጭራሽ ቢሯቸው አካባቢ አያስጠጉንም፡፡ በዚህ ችግር ያለባቸው ተቋማት አሉ፤ ይህ መስተካከል አለበት፤ በዚህ ሂደት መከላከያን ላመሰግን እወዳለሁ፤ አንዳንድ ተቋማት ተከታትለው እራሳቸው ይከፍላሉ፡፡ የተወሰኑት ላይ ደግሞ ችግር አለ እንጂ በውጭ ተቋማት ላይ ችግር የለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የመብራት መቆራረጥ ዛሬም ችግር ሆኖ ዘልቋል፤ ከተለመደው ምላሽ ውጭ ዘላቂ መፍትሔ ምንድን ነው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** የተለመደ መልስ አንሰጥም፤ ለሕዝብ የኃይል መቆራረጡን ከመነሻው ለማስረዳት ያህል የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ደካማ ነበር፡፡ 1990ዎቹ ላይ የነበረን 400 ሜጋዋት ኃይል ነው፡፡ ስለዚህ መንግሥት ለኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ቅድሚያ ሰጥቶ ሠርቷል፡፡ ከየትኛውም ሴክተር በበለጠ ሀብት የፈሰሰው ኤሌክትሪክ ላይ ነው፤ በዚህም አሁን አምስት ሺህ ሜጋዋት አለ፤ ዛሬ ከሁለት ዓመት በኋላ አስር ሺህ ሜጋዋት ይደርሳል፡፡ ከእኛ ተርፎ ለጎረቤት ሀገራት ሊሆን የሚችል ኃይል አለ፡፡ በዚያው ልክ በማከፋፈያ ከተሞች አካባቢ ያለው የማከፋፈያ ኔትዎርክ አልተሠራም፡፡ ምክንያቱም ቅድሚያ ለኃይል ግንባታ በመሰጠቱ ነው፡፡ ወደ ከተሞች አካባቢ ደግሞ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በተጠናከረ ሁኔታ እየሠራን ነው። በአዲስ አበባ ሁለት ምዕራፍ ፕሮጀክት ተጠናቋል። በአጠቃላይ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር የመካከለኛ ቮልቴጅ፣አምስት ሺህ ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ እንዲሁም አስር ሽህ አምስት መቶ የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮች አሉ፡፡ እነዚህ ያረጁ ናቸው፤ ሌላ



ነገር ብናወራ ጥቅም ስለሌለው ወይም ደግሞ ይህን ኔትዎርክ በሙሉ በአንድ እና በሁለት ዓመት በማሻሻል እናጠናቅቅ ቢባል የማይቻል ስለሆነ ከእውነት ውጭ እንሆናለን፡፡ ፋይናንስ ከማግኘት ጋር ሆነ መሬት ላይ ከመተግበር ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል የሠራናቸው የማሻሻያ ሥራዎች ቢኖሩም፤ በባቡር ዝርጋታ ምክንያት ቀደም ሲል የተዘረጉ መስመሮች ተበጣጥሰዋልና ከአሮጌ ኔትወርክ የጀመርነው ለዚህ ነው፡፡ አንደኛ በኃይል ግንባታ ላይ ቅድሚያ ስለተሰጠ፣ ሁለተኛ ከ2003 እስካ 2011 ድረስ በሜቴክ ምክንያት የዕቃ አቅርቦት እጥረት በመኖሩ የነበረው ቃል በቃል ያረጀ ኔትወርክ ነው፡፡ 2011 ዓ.ም ላይ ይህን ሁለት ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር የመካከለኛ ቮልቴጅ፣ አምስት ሺህ ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ እንዲሁም አስር ሽህ አምስት መቶ የማከፋፈያ ትራንፎርመሮችን ስትራቴጂ በመቅረፅ በአራት ምዕራፎች ተደራሽ ለማድረግ ፕሮጀክት ተነደፈ፡፡

የመጀመሪያው ፕሮጀክት የስምንቱ ከተሞች ፕሮጀክት ይባላል፡፡ 2011 ዓ.ም ላይ ተጀምሮ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀው በ2013 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት የክልል ዋና ዋና ከተሞችንና አዲስ አበባን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በዚህ ሥራ የተሻሻሉት አዲስ አበባ ላይ 40 ኪሎ ሜትር መካከለኛ ቮልቴጅ፣ 412 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፣ 82 የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮችና 15 switching station ናቸው፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ በ2012 ዓ.ም ተጀምሮ 2014 ዓ.ም ላይ ተጠናቀቀ። በዚህ ደግሞ በዋናነት የተሰራው 725 ኪሎ ሜትር የመካከለኛ ቮልቴጅ፣ 400 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፣ 400 አጋዥ የማከፋፈያ ትራንፎርመርና 73 switching station ነው፡፡ ሁለተኛው ፕሮጀክት የተሠራው በቻይና መንግሥት ድጋፍ ሲሆን፣ እሱም ተመርቆ አገልግሎት ጀምሯል፡፡ ሦስተኛው ምዕራፍ በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ወጪ ተደርጎ የተጀመረው ባለፈው በጀት ዓመት ነው፡፡ በዚህ የበጀት ዓመት መጨረሻ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቅ የነበረ ቢሆንም በኮሮና እና በሌላም ምክንያት ሳይጠናቀቅ ቆይቷል። በዚህ ሥራ ደግሞ 733 ኪሎ ሜትር መካከለኛ ቮልቴጅ፣ 400 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፣ 258 አጋዥ የማከፋፈያ ትራንፎርሜሮች፣ ሰብ እስቴሽኖችና የመቆጣጠሪያ ጣቢያ ጨምሮ አሁን እየተሠራ ነው፡፡ ይህም በ2016 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡

የዚህ ስትራቴጂክ ዕቅድ አራተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ 600 ኪሎ ሜትር መካከለኛ ቮልቴጅ፣ ቀሪውን በሙሉ ማለት ነው፣ 2000 የማከፋፈያ ትራንፎርመሮች ያሉት በ2017 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡ የአማካሪ ቅጥርና የጫረታ ሂደት ተጀምሯል፡፡ እየተሠራ ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሥራ ነው፡፡ ለምሳሌ የመስመር ዝርጋታው በመሬት ስር ይካሄደል፤ የሚሠራው ኮንክሪት ምሰሶ ነው፡፡ የምንጠቀመው ሽፍን ሽቦ ነው፡፡ ይህ የኃይል መቆራረጡን ይቀርፋል፡፡ በዚህ በተዋቀረ ፌዝ አሮጌውን ኔትዎርክ ለመቀየር እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መብራት በአንድ አካባቢ መንገድ ከፍሎ ይጠፋል፤ ይህ ስምንድነው የሚፈጠረው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** ይህ የሚሆነው አንደኛው ትራንስፎርመር አገልግሎት የሚሰጠው ለተወሰነ ደንበኛ ነው፡፡ እሱ ላይ ችግር ሲፈጠር ሰፈሩ መብራት ያጣል። እስኪጠገን ድረስ በዛ መስመር ብልሽት ካለ መስመሩ አገልግሎት አይሰጥም፡፡ ሌላው ግን ያገኛል፡፡ እና በዚህ ምክንያት በኔትወርኩ ነባራዊ ሁኔታ የሚፈጠር ነው። በአካል ሄደን አይተናል፡፡ ማሻሻያ ያደረግንባቸው መስመሮች በሰሞኑ የአየር ሁኔታ እንኳ አልተጎዱም፤ እና በዚህ ስትራክቸርድ በሆነ ፌዝ እየሠራን ነው፡፡ ነገር ግን ሥንሰራ ችግሮች ያገጥሙናል፡፡ የከተማው ማስተር ፕላን አሁን እየተተገበረ ነው፤ እነዚህን ኔትዎርኮች አንሱ የሚል ይመጣል፤ እርሱን እናነሳለን፤ ይህ ችግር ነው። በመሠረተ ልማት የሚቆራረጡ ደግሞ አሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ነው እንጂ ብዙ ሥራ እየሠራን ነው፡፡ ይሁንና በብዙ ምክንያት በአንድ ምሽት ችግሩን መቅረፍ ደግሞ አንችልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ዘላቂ መፍትሔው ምንድነው?**

**ዶክተር ገበየው፡-** ዘላቂ መፍትሔው 2017 ዓ.ም ላይ በሚጠናቀቀው ፕሮጀክት የሚገኝ ነው፡፡ ሰሞኑን የተከሰተው የኃይል መቆራረጥ ደግሞ ባልተጠበቀ የአየር ሁኔታ የመጣ ነው፡፡ ሁለተኛውና ትልቁ ችግር አራቱንም ምዕራፍ ሥንሰራ አሮጌውን መስመር በአንድ መንገድ ላይ ትተን በሌላው አይደለም የምንሠራው፡፡ ኮሪደር የለም፤ ከተማ ውስጥ እያጠፉን ነው ሌላውን የምንሠራው በዚህ ምክንያት ኮንክሪት ተክለን እስኪደርቅ እንጠብቃለን፣ እንሱሌተር እናሥራለን ያኔም ይጠፋል እና ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈፀም ሲባል የሚጠፋው ኤሌክትሪክ ነው የሚበዛው በእቅድ ላይ የተመሠረተ የኃይል መቆራረጥ ነው ያለው፤ ይሄ ሲኖር ደግሞ በሁሉም የሚዲያ አማራጮች ለኅብረተሰቡ እናሳውቃለን፤ ትልቁ ለኃይል መቆራረጡ ምክንያት በእራሳችን የሚሠሩ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በብዛት ከኅብረተሰቡ የሚነሳው ጥያቄ ከሌሎች የመሠረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ጋር በመናበብ ያለመሥራት ችግር ነው፤ አንዱ የሠራውን ሌላው ያፈርሳል በሚል እርስ በእርስ መወቃቀስም አለ፤ ከዚህ አኳያ የቅንጅት አሠራራችሁ ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ገበየው፡-** አዲስ አበባ ውስጥ አዲስ ማስተር ፕላን አለ፤ በጣም አሮጌ ሰፈሮች እንደገና ፈርሰው የሚሠሩ አሉ፡፡ መሠረተ ልማት ገና እየተስፋፋ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ ደግሞ ቴሌ፤ ውሃና መብራት ይኖራል፡፡ ይህ ካልተቀናጀ ሊመራ አይችልም፡፡ ከአዲሱ የመንግሥት ሪፎርም በፊት ከ2006 እና 2007 ዓ.ም ጀምሮ አዳዲስ በሚሠሩ መንገዶች ላይ በሙሉ ነበር። አሁን ቅንጅቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ የመሠረተ ልማት ቅንጅት የሚባል ተቋም አለ፤ በዚህ መልኩ በተሠራው ሥራ ለውጥ ታይቷል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ችግሩ ግን አሁንም እንዳለ ነው፤ አልተቀረፈም፤ ስምን?**

**ዶክተር ገበየው፡-** አዎ! በዋናነት ያለው ሁለት ችግር ነው፡፡ የቅንጅት ችግር አይደለም፤ ለምሳሌ ለቡ ማሳለጫ አሁን ደግሞ ኢምፔሪያል ሲሠራ የእኛ መስመር ተቆርጦ ተነስቷል፡፡ ይህ ደግሞ ብንቀናጅም ሆነ ባንቀናጅም የግድ መሆን ያለበት ነው፡፡ እኛ ያንን መስመር የዘረጋነው 2000 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ነው፤ ከገርጂ ማከፋፈያ ወደ ቦሌ ያለው ማሳለጫ ይመጣል የሚል ነገር አልነበረም፡፡ አሁን መጣ፤ ሽቦውን ወይም መስመሩን ማንሳት ግዴታ ነው፡፡ ማንሳት ደግሞ አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም አንደኛው የቦታ ነው። ኮርደሩ እዛው ላይ ነው፡፡ መንገዱን ሲጨርሱ ያንን ሠርተውልን ያልፋሉ፡፡ እዛ ውስጥ መልሰን በሌላ ሽቦ እንቀብራለን፡፡ ሁለተኛው የጊዜ ችግር ነው፤ እነዚህ ሽቦዎች የተሠሩት በሀገር ውስጥ አይደለም፤ የውጭ ምንዛሪ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ቅንጅት በመጥፋቱ የመጣ አይደለም፡፡ ይህም በዚህ ተቋም ገፅታ ላይ አሉታዊ አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡

ሌላው በዚህ የቅንጅት አሠራር ውስጥ ያልተቀረፉ ተቋማት አሉ፤ ሁሉን በዚህ ውስጥ ማካተት አይቻልም። መሠረታዊ የሆኑ የመሠረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ናቸው ያሉት፡፡ በዚህ ያልተቀረፉ አጥርና መሰል ሥራዎችን በሚሠሩ ተቋማት ደግሞ የሚፈጠሩ ችግሮች እና ጉድለቶች አሉ፡፡ በመሠረታዊነት መሻሻል የሚገባው ነገር ቢኖረውም ችግሩ እየተፈጠረ ያለው የግድ በሆኑ ጉዳዮች ነው፡፡ አሁን በጣም ፈታኝ የሆነብን ከመቶ ኪሎ ሜትር በላይ መስመሮችን እናነሳለን፤ ለአዲስ አበባ መንገዶች ፕሮጀክት ሥራና በመሬት ውስጥ ሲሆን ደግሞ ከባድ ነው፡፡ በጣም ከባድ ፈተና የሆነብን ይህንን ማንሳት ነው፡፡ ስለዚህ በዕቅድ ወቅት ለዚህ ትልቅ ትኩረት ቢሰጥ የተሻለ ነው፡፡ በዕቅድ ደረጃ የማቀድ አይነት ጉድለቶች ግን አሉ ብለን ለመሥራት ግን አቅም እያጠረን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በተቋሙ የሠራተኛ ሥነ ምግባር ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ገበየው፡-** እዚህ መሥሪያ ቤት የገባሁት 1995 ዓ.ም ነው፡፡ በሥነ ምግባር ጥሩ የሆነ ተቋም ነው የነበረው፤ ያኔ የነበረው እሴት እኔ ዘንድ ቀርቷል። እኔ የዲስትሪክት ሥራ አስኪያጅም ነበርኩ፡፡ 1998 ዓ.ም አካባቢ የሥራ የተቋም ፍቅር እንጂ የሥነ ምግባር ችግር አልነበረም፡፡ በመሠረታዊነት ችግሮች መፈጠር የጀመረው በተደጋጋሚ እንዳነሳሁት 2002 እና 2003 ዓ.ም ነው፤ ከውጭ የሚገባውን ምርት እንዲተካ ታስቦ ሜቴክ ተቋቋመ፡፡ ግን በወቅቱ በማኔጅመንት ችግርና በተለያዩ ምክንያቶች እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ዕቃ በተገቢው አልቀረበልንም፡፡ አሁን ይህ እጥረት የሥነ ምግባር ችግር ፈጥሯል የሚል ግምገማ አለን። የሚመጣው የተወሰነ እቃ ነው፡፡ እዛ ላይ ብዙ የመሽቀዳደም ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ አንድ ምክንያት ይሆናል፤ አሁን ይህንን በመሠረታዊነት የምንፈታበት ሥርዓት ተዘርግቷል። ደንበኛ እና ሠራተኛ እንዳይገናኝ ደግሞ እየሠራን ነው፡፡ በሲስተም ደንበኛ ቤቱ ቁጭ ብሎ አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ የሚፈጥር ሥርዓት እየተዘረጋ ነው። ይህ ሁሉ በመሠረታዊነት ችግሩን ለመፍታት፡፡

ሌላው በአራቱ ቅርንጫፎች ስር በሚገኙ በሠላሳ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሥነ ምግባር ክበባት ተቋቁመዋል። የሚመሩት ጥሩ ሥነ ምግባር ባላቸው ሠራተኞች ነው። በዚህ ሂደት በተሠራው ሥራ ለውጦች አሉ፡፡ ሙሉ በሙሉ ግን ችግሩ አልተቀረፈም፡፡ ይሄንን ሁሉ አልፈው በሚያጠፉት ላይ ምሕረት የሌለው የዲሲፕሊን ቅጣት ይወሰዳል፡፡ በመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አንድ መቶ ዘጠኝ ሠራተኞችና አመራሮች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 15 ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ስንብት፣ 38 ሠራተኞች ላይ እስከ አራት ወር የደመወዝ ቅጣት፣ 16 ኃላፊዎች ላይ ደግሞ ከኃላፊነት መነሳት፣ 14ቱ ላይ የቃል ማስጠንቀቂያ፣ 26 ሠራተኞች ደግሞ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተቋሙን ወደ ዘመናዊ ተቋም ለመለወጥ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ላነሳናቸው ጥያቄዎች ስሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶክተር ገበየው ሲካሳ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው።የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል።ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል።በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ጥንታዊው የሀገሬ “የዘመናዊ ዴሞክራሲ” መገለጫዎች

### “ነገርን ከሥሩ…፤

የዚህ ጽሑፍ ዋና ርዕስ ቀድሞ ካልተብራራ በስተቀር ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች እየተመዘዙ ሊያከራክሩ እንደሚችሉ እንገምታለን። “ጥንታዊ” ተብሎ “ዘመናዊ ዴሞክራሲ” መባሉ ተቃርኗዊ (Paradox) ይሉት ዓይነት ጥያቄ አያጭርም ወይ? በአሚጋችነቱ የተገመተ የመጀመሪያ ስጋት ነው። “ጥንታዊ ሲባልስ የዘመን ወሰኑ ወደ ኋላ ምን ያህል ያፈገፍጋል? ጥርት ያለ የዘመናዊ መስፈርትስ ምንድን ነው?” እነዚህ ጥያቄዎች መመለስ የሚገባቸው በዚህ ጽሑፍ ዐውድ መሠረት ስለሆነ በአጫጭር ብያኔዎች ቀድመን ይዘታቸውን መወሰኑ አስፈላጊ መስሎ ታይቶናል፡፡

ጥንታዊ፡- የሚለው ቃል የሚወክለው የዛሬ መቶ ዓመት ግድም የነበረውን የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ “ዘመናዊ ዲሞክራሲ” መሰኘቱ ደግሞ የዛሬው “ዘመናይ ፋሽን ተከታይ ዴሞክራሲያችን” ከፖለቲካችንና ከሕዝባችን ጋር በየውሎ አምሽቶው ሲጋጭ እንደምናስተውለው ሳይሆን የዚያ ዘመን የሕዝብ ጥያቄዎችና መንግሥታዊ ውሳኔዎች የተስተናገዱበትን “ነባር ጥበብ” ለማስታወስ በማስፈለጉ ነው፡፡

ወደ ዋናው መዳረሻችን ከመገስገሳችን አስቀድሞ ከምንተነፍሰው ዓየር ባልተናነሰ በየሴኮንዱ ስሙን እያነሳን የምንጥለውን “ዴሞክራሲ” የሚለውን የተውሶ ጽንሰ ሃሳብ በዕድሜው ርዝመት “የጃጀና ያፈጀ” ሊባል እንደሚችል አስታውሶ ማለፉ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ከጥንታዊቷ ግሪክ የፖለቲካና የፍልስፍና ማህጸን ውስጥ “ነፍስ ዘርቶ” እስከ ዓለም ዳርቻ የተበተነው “ዴሞክራሲ” የሚለው ቃል ከሁለት መንታ መሠረታዊ ቃላት የተዋቀረ ነው፡፡ ዴሞስ (dêmos) የሚለው አንዱ ጽንሰ ሃሳብ ተራና ሠርቶ በሌ የሆኑ የግሪክ ዜጎችን ለማመልከት ሲሆን፤ ክራቶስ (krâtos) የሚለው ሁለተኛው መንትያው ደግሞ ኃይል ወይንም ብርታትን (force/might) ይወክላል፡፡ በአጭሩ ሁለቱ ቃላት ሲገጣጠሙ “የሕዝብ ኃይል/ብርታት” የሚለውን ሃሳብ መሸከሙን እናረጋግጣለን። አንዳንዶች “የሕዝብ አስተዳደር” የሚል አፈንጋጭ ፍቺ ሲሰጡትም እያስተዋልን ነው፡፡

ቅድመ ልደተ ክርስቶስ (508 ዓ.ዓ) የኖረውና በአቴናዊያን ሕገ መንግሥት ሪፎርም ላይ ደማቅ አሻራውን ያሳረፈው ክሊስተንስ (Cleisthenes) የጥንታዊቷ ግሪክ/አቴንስ የዴሞክራሲ አባት እየተባለ በታሪካቸው ይዘከራል፡፡ ፈረንሳይና አሜሪካን ደግሞ “የዘመናዊ ዴሞክራሲ” ቀዳሚ ተለማማጆች እየተባሉ ይጠቀሳሉ፡፡ “ዘመናዊነት” በምን መስፈርት? የየሀገራቱ ፖለቲከኞችና እኛ የሩቆቹ ዘመናዊነትን የምንበይነው ለየቅል ስለሆነ አንባቢው የራሱን ድንጋጌ ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

### ታሪክ ቢያረጅም፤ አሻራው አይደበዝዝም፤

ወደ ራሳችን ጉዳይ መለስ የምንለው ከታሪካችን ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች መካከል አንድ መሪ ሃሳብ ቃል በቃል በመጥቀስ ይሆናል፡፡ የታሪካችን መሰዊያ “ፍምም አመድም” እንዳለው እሁድ ሚያዝያ 1 ቀን 2015 ዓ.ም በዚሁ አንጋፋ ጋዜጣ ላይ በጻፍኩት ጽሑፍ ውስጥ በዝርዝር ማብራራቴን ልብ ይሏል። እንቀጥል። “በ1909 ዓ.ም መስከረም 17 ቀን ሕዝብ ተሰብስቦ አቤቶ ኢያሱን ሽሮ ከመንግሥት ባስወጣቸው ጊዜ ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ተብለው የአባታቸውን የዳግማዊ ምኒልክን ዙፋን እንዲወርሱ፤ እንዲሁም የሐረሩ ገዥ የልዑል ራስ መኮንን ልጅ ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን (በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ) ‹ራስ› ተብለው አልጋ ወራሽና እንደራሴ እንዲሆኑና የመንግሥቱን ሥራ እንዲፈጽሙ የሕዝቡ ጉባዔ ወሰነ፡፡” (የታሪክ ማስታወሻ፤ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፤ ገጽ 32)፡፡ “ሕዝበ ውሳኔ” የሚለው ገለጻ “በዘመናዊ የዴሞክራሲ” ዲስኩር ውስጥ ተደጋግሞ እንደሚነሳ አንባቢው ልብ ይበል፡፡

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን ለ46 ዓመታት ያህል ከመሩ በኋላ አካልን ሽባ በሚያደርግ (ፓራላይዝድ) በሽታ ተለክፈው አልጋ ላይ በዋሉበት ወቅት የመንግሥታቸው ወራሽ እንዲሆኑ የመረጡት የ12 ዓመቱን የልጃቸውን ልጅ ኢያሱን ነበር፡፡ ከእርሳቸው ህልፈት በኋላም መንበረ ሥልጣኑን የተረከቡት አቤቶ ኢያሱ የዘመኗን “ታላቅ ሀገር ኢትዮጵያን” በአግባቡ ለመምራት ልጅነትና ቅብጠት ፋታ ስላልሰጧቸው ከላይ እንደተገለጸው ሹም ሽር ተካሂዶ ሥልጣነ መንግሥቱ የተሸጋገረው ወደ ንግሥት ዘውዲቱ ነበር፡፡

“ወይ ያለመታደል!” እንዲሉም ከኢያሱ ወደ ዘውዲቱ የተላለፈው መንበረ ሥልጣን እንደ አባታቸው ዘመን በአንፃራዊ መልኩም ቢሆን የረጋና የተረጋጋ መሆን አልቻለም ነበር፡፡ ንግሥቲቱ ሥልጣን ላይ በወጡ በወሩ የልጅ ኢያሱ ወላጅ አባት ንጉሥ ሚካኤል “እንዴት በልጄ ዙፋን ላይ መፈንቅለ መንግሥት ይደረጋል?” በማለት ከወሎ ግዛታቸው ጦራቸውን እየሰበቁ ሠራዊታቸውን ወደ መሃል ሀገር በማዝመት መጀመሪያ ኮረማሽ ላይ በተደረገው ውጊያ በለስ ቀንቷቸው ነበር። ወደ ፊት በመገስገስም ዙፋን ለመናድ ሰገሌ ላይ ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ.ም በተደረገው ውጊያ ተሸንፈው እጃቸው መያዙ በታሪካዊ ሰንዶቻችን ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

በዚሁ ጦርነት ላይ እርስ በእርስ ሲዋጉ የወደቁት ታላላቅ የጦር መሪዎችና ለፎው (ተርታው) ሠራዊት ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ ደግሞም እኮ በመገዳደልና በመጠፋፋት ማን እኛን ይስተካከላል? ለመሆኑ በእርስ በእርስ ፍልሚያ ሞት ያላዘመርንበት ሥርዓተ መንግሥት ይኖር ይሆን? በግሌ እንጃ፡፡

ለማንኛውም ምርኮኛው ንጉሥ ሚካኤል እጃቸው ተይዞ አልጋ ወራሹ ባሉበት ወደ ንግሥት ዘንድ ሲቀርቡ አቀባበል የተደረገላቸው ንግሥቲቱና አልጋ ወራሹ አክብሮታቸውን ለመግለጽ እንደቆሙ “ጌታችንና አባታችን እንደምን ወደዚህ ስህተትሊገቡ ቻሉ?” በሚል ቁጭት አክብሮታቸው ዝንፍ ሳይልና የወጉና የማዕረጉ ክብር ሳይጓደልባቸው ነበር፡፡ የዚያን ወቅት መሪዎች የነበራቸው የልብ ስፋት ምን ያህል ታላቅ እንደነበር ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡

ከንጉሥ ሚካኤል ጋር የተደረገው ጦርነት ካበቃ ከስድስት ወራት በኋላ “የመሐል ሠፋሪ” በሚባለው የጦር ክፍል ቆስቋሽነት ከፍ ያለ አድማ ተከናውኖ ነበር። ሰበበ ምክንያቱ በታሪካችን በርካታ መዛግብት ውስጥ እንደሚከተለው ተጠቅሶ ይነበባል፡፡ “ደጉ ንጉሣችን አጼ ምኒልክ 12 ሚኒስትሮችን መርጠው ቢሾሙልን ለሀገር ልማት፣ ለሕዝብ አንድነት በመምከር ፈንታ አንዱ ለአንዱ የየራሳቸውን ጥቅም በመመልከት ሀገሩን አበላሹት እንጂ ለመንግሥት የጠቀሙትና የሠሩት ጉዳይ የለም፡፡”

በክሱ ውስጥ ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ማሳያዎች መካከል ሁለቱ ክሶች እንደሚከተለው ተመዝግበዋል። “የሥራ ሚኒስትር ተብሎ የተሾመው የራሱን ቤት ለመሥራት በቤት ላይ ቤት እየቀጠለ (ፎቅ ለማለት ሳይሆን አይቀርም) ወደ ሰማይ ለመውጣት ይገሰግሳል። እንደዚሁም የግቢ ሚኒስትር የተባለው የራሱን ሀብት ብቻ በማደራጀቱ ከምኒልክ ቤት ለግብር የሚሆን መሰናዶ ታጥቶ ባለፈው ሰሞን ከእርሱ ቤት ዱቄት ተግዞ ተሠናዳ፡፡ 12ቱ ሐዋርያት ተብለው ‹በምኒልክ› የተሾሙት ሚኒስትሮች በሙሉ 12 አጋንንት ሆነው አረፉት፡፡ የአድመኞቹ ጥያቄ ፈጣን መልስ አግኝቶ ከ12ቱ ሚኒስትሮች መካከል የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ብቻ ሲቀሩ አሥራ አንዱ ተሽረው ወደ ርስት ሀገራቸው እንዲሄዱ ተወሰነና እየታዘዙ ሄዱ” (የታሪክ ማስታወሻ ገጽ 57 - 63)፡፡

“የሕዝብ ድምጽ፤ የእግዜር ድምጽ” ይሏል እንዲህ ነው፡፡ ይህንን መሰል ከባድ የሕዝብ ጥያቄ ሳይውል ሳያድር የዛሬዎቹ ዘመናይ “የዲሞክራሲ መንግሥታት” መሪዎች በዚህ አግባብ ጨክነው የሕዝባቸውን እምባ ለማበስ ይችሉ ይሆን? መልሱን ለመስጠት አንባቢው ከራሱ ጋር ቢሟገት የሚሻል ይመስለናል፡፡ በዚህ ጸሐፊ እምነት ግን ይህ ድርጊት እጅግ ዘመናዊ የዴሞክራሲ እርምጃ እንደሆነ ከልቡ ያምናል፡፡

ከዚሁ ከሚኒስትሮች ሽረትና ሹመት ጋር የተገናኘው ዋና ጉዳይ የአማካሪዎች አስፈላጊነት ነበር። ታሪኩ እንዲህ ይጠቀሳል፡- “በዓለም ያሉ ነገሥታት ሁሉ ይልቁንም ከሚኒስትሮች ሌላ መካር (አማካሪ) የሚያስፈልግ መሆኑ ስለሚታመንበት ከየሀገሩ ሽማግሌ 300 እና 500 የሚሆኑ የሀገር ጨዋ ተመርጠው ይሾሙ ነበር፡፡” ዴሞክራሲያችን ሆይ ትሰማለህ? “መካሪ የሌለው ንጉስ ያለ ዓመት አይነግሥ!” የሚለውን የብሂላችንን ሥጋት የተሻገረ አመራር ይሏል እንዲህ ነው፡፡

ብዕረ መንገዳችንን የአማካሪዎች ወሳኝ ሚና የተስተዋለበትን አንድ ታሪካዊ አጋጣሚ ጠቅሰን እንለፍ። ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ የሲዳሞ ገዥ በነበሩበት ወቅት ሎሌዎቻቸው እየከዱ ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን መግባታቸውን ያስተዋሉት አንጋፋው አርበኛ መገፋታቸውን ለመበቀል በማሰብ ከሲዳሞ ግዛታቸው እየተንደረደሩ አዲስ አበባ ቤታቸው ይገባሉ። ነገረ ሥራቸው ሁሉ ለደግ ያለመሆኑን የጠረጠሩት የመንግሥቱ አማካሪዎች ከፉኛ የተቆጡትንና አዲስ አበባ በሚገኘው ቤታቸው ሽፍተው በራቸውን ከውስጥ በመቆለፍ ያገነገኑትን አዛውንት በኃይል ርምጃ እልሃቸውን ለማብረድ ከመሞከር ይልቅ ውጥረቱ እንዲፈታ የተደረገው በሚከተለው ጥበብ የተሞላበት አያያዝ ነበር፡፡

“ደጃዝማች ባልቻ ከሲዳሞ ጦራቸውን አስከትለው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ እቤታቸው በመሸፈት ቢጠሯቸው አልመጣም ብለው በእምቢታቸው ጸኑ። ...ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ብዙ ሽማግሌ አማካሪዎች ተሰብስበው ነገሩ በእርጋታ እንዲታሰብበት እንጂ የእሳቸውን ድርጊት ተከትሎ የኃይል ርምጃ እንዳይወሰድ ተመከረና ጉዳዩ በርጋታ ተያዘ፡፡” - ይህን መሰሉ መንግሥታዊ እርምጃ ከፍ ያለ የብስለት ደረጃ የተስተዋለበት እንጂ ሌላ ምን ስያሜ ሊሰጠው ይችላል?

የደጃዝማች አባውቃው ብሩ ታሪክም ቢጠቀስ ጠቃሚ እውቀት ሊያስጨብጥ ስለሚችል ቆንጥረን እናስታውስ፡፡ የቤተመንግሥቱ የዘበኞች አለቃ (በቀድሞ አጠራር የክብር ዘበኛ፤ በዛሬው የእኛ ዘመን ሪፐብሊካን ጋርድ እንደምንለው) የነበሩት አባውቃው ብሩ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን የንግሥት ዘውዲቱን ሥልጣን ለመገልበጥ ውስጥ ለውስጥ ያሴራሉ የሚለውን ሃሜት እንደ እውነት በመቁጠር ሊፋለሟቸው ይነሳሉ፡፡ ይህ የመጠፋፋት ዝግጅት ወሬ የደረሳቸው ንግሥቷና አልጋ ወራሹ ራሳቸው “ሃሜቱ ሀሰት መሆኑን” ለማስረዳት በተደጋጋሚ ሽማግሌዎችን ከአባውቃው ዘንድ በመላክ ነገሩን ለማርገብ ቢሞክሩም ሊሰሟቸው አልወደዱም። በመሆኑም ንግሥቲቱ ሊወስዱ የተዘጋጁበት እጅግ አስገራሚና አስደናቂ ውሳኔ እንዲህ ተመዝግቧል፡፡

“...ንግሥትም የክብርን ነገር ሳይመለከቱ የጊዜውን ጸጥታ መጠበቅና ደም የሚያፋስስ ነገር እንዳይደርስ በማሰብ አባውቃው ወዳሉበት ሥፍራ ለመሄድ ታጥቀው ተነሱ፡፡... ከንግሥት ከራሳቸው ቃል ካልሰማሁ ካለ በዚህ ምክንያት ተኩስ ተነስቶ ደም ከሚፈስ የንግሥት መሄድና ነገሩን ማብረድ መልካም ሃሳብ ነው፤ ሲሉ ሽማግሌዎቹ አማካሪዎችም ተስማሙ፡፡”

ታሪኩ እጅግ ረጅምና ውስብስብ ስለሆነ የተጠቀሰው ጥቂቱ ብቻ ነው፡፡ ውሳኔውን የሰሙት አልጋ ወራሹ ማፋረሻ ምክንያት በመስጠት ንግሥት ዘውዲቱ ወደተባለው አማጺ ዘንድ ባይሄዱም ውሳኔያቸው ግን እጅግ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ነበር፡፡ “ለክብሬ ብዬ የንጹሐን ደም እንዲፈስ ስለማልፈልግ እኔው ራሴ ሄጄ ነገሩን አበርደዋለሁ...” ዋው! እንደምን ብስለትና ርህራሄ የተስተዋለበት ውሳኔ ነበር፡፡

ብዙ መሰል ተግዳሮቶች የተስተናገዱበትን የዚያን “የጥንታዊ ዘመን” ሀገራዊ ፈተናዎች “የዛሬይቱ ዘመናይ ኢትዮጵያ” ልቧን ከፍታና ታሪኳን አክብራ ብዙ ጥበቦችና እውቀቶች መማር ብትችል በእጅጉ የምታተርፍ ይመስለናል፡፡ በከባድ አውሎ ነፋስ በሚንገላታ ጀልባ የምትመሰለው ሀገሬ፣ በነጋ በጠባ ቁም ስቅሏን ስታይ መመልከት የእኛን የዜጎቿን ልብ በሀዘን መስበሩ፤ እርሷም ዕድሏ ባሸከማት ዕጣ ፈንታ ጎብጣ ቀና ማለት ያለመቻሏ ለእኛ ብቻ ከፈጣሪ የተወሰነብን ፍርጃ እስኪመስል ድረስ እነሆ እህህ እንዳልን ዘመናችንን በመግፋት ላይ ነን፡፡

ቢቻልና ቢሆንልንማ ኖሮ የጥንት ጥንት ግሪካዊያን ያወረሱንን “ካብ አይገባ የጃጀ ዴሞክራሲ የሙጥኝ ብለን እየተደናቆርን” ዕድሜያችንን በሀዘን ከምንገፋ ይልቅ “የተውሶውን ፍልስፍና” ሰንዱቅ ውስጥ በመቆለፍ ከሀገር በቀል ታሪኮቻችንና እወቀቶቻችን ጥበብ እየቀዳን መከራችንን ብናቀለው በእጅጉ በተጠቀምን ነበር፡፡ እስከ መቼስ መንግሥት ወዲያ ማዶ፤ ሕዝብ ወዲህ ማዶ ሩቅ ለሩቅ ቆመው እየተያዩ በተመሳሳይ የጋራ ሀገራዊ አጀንዳ ላይ አብሮ ከመጓዝ ይልቅ መጓተት እየመረጥን እንደተገፋፋን ዘመናችንን እንጨርሳለን? ኢትዮጵያ ሆይ መከራችን ለአንቺም ሆነ ለእኛ ለዜጎች ስለማይጠቅመን አንቺም ወደ ቀልብሽ ተመለሺ፤ እኛም ወደ ሩሐችን እንመለሳለን፡፡ ጽናቱን ይስጥሽ ሀገሬ! ሰላም ለሕዝባችን ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

# የበዓል ገበያና ዋጋ የማረጋጋት ዝግጁነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በክርስትና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበረው የእየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤ በዓል መጣሁ መጣሁ እያለ ነው፡፡ በዓሉ በመጪው እሁድ የሚከበር መሆኑን ተከትሎ የእምነቱ ተከታዮች በዓሉን ለማክበር ዝግጅቶችን እያደረጉ ናቸው፡፡ ለእዚህም ሁሉም እንደየአቅሙ ለግብይት መውጣት ጀምሯል፡፡

እኛም ለበዓሉ ድምቀት አንዱና ዋናው ጉዳይ የሆነውን የግብይት ሂደት በመቃኘት የሸማቹና ነጋዴውን እንቅስቃሴ፣ ለመረዳት በቅድሚያ በአዲስ አበባው ሾላ ገበያ ተገኝተናል፡፡ አቶ ሙሉጌታ አሰፋን በዚሁ ገበያ አገኘናቸው፡፡ ገበያ እንዴት ነው ስንል የጠየቅናቸው አቶ ሙሉጌታ ‹‹ሕዝቡ የኑሮ ውድነቱ ከትዕግስቱ በላይ ሆኗል›› ሲሉ መለሱልን፡፡ ኑሮ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የከበዳቸው አሁን መሆኑን አቶ ሙሉጌታ ተናግረዋል፡፡ አንድ ኪሎ ሽንኩርት 50 ብር፣ ድንች 30 ብር፣ ቲማቲም 35 ብር ካሮት 30 ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑንና ዋጋው በጣም ውድ መሆኑን ነው የገለጹት፡፡ እኛም በገበያው ላይ የታዘብነው ይህንኑ ነው፡፡

አቶ ሙሉጌታ ጡረተኛ መሆናቸውን ገልጸው፣ የኑሮ ውድነቱ ከአቅማቸው በላይ እየሆነ መምጣቱን ጠቁመዋል። መንግሥት ጡረተኞችን ቢያስብና ገበያውን ማረጋጋት ቢችል መልካም መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በተለይም በእንዲህ አይነቱ የበዓል ወቅት ገበያን ማረጋጋት ከመንግሥት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ስማቸው የተቀየረው ነጋዴው አቶ ከበደ ናደው እህል በረንዳ ሄደው የሚፈልጉትን ያህል እህል ማግኘት እንዳልቻሉ ይናገራሉ። የዋጋ ንረቱን ያስከተለው የአቅርቦት እጥረት እንደሆነም ጠቅሰው፣ እጥረቱም የተከሰተው በየኬላው ባለው ችግር ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት እህል ከየአካባቢው እየገባ አይደለም የሚሉት አቶ ከበደ፣ እህል በነጻነት ከየአቅጣጫው እንደበፊቱ መግባት ቢችል የሚታየውን የእህል አቅርቦት እጥረት ማቃለል ይቻላል ባይ ናቸው፡፡

እህልን ጨምሮ ማንኛውም የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ በተለይም በበዓል ወቅት ተፈላጊና አስፈላጊ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ከበደ፤ አሁን ገበያው ላይ የሚታየው የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም መሆኑን ይገምታሉ፡፡ ቀን በቀን በሚለዋወጥ ዋጋ ሸማቹ ብቻ ሳይሆን ነጋዴውም ጭምር እንደተቸገረም ነው የገለጹት፡፡ በዕለቱ ያለውን ዋጋ በመግለጽም ዛሬ ያለው ዋጋ ነገ ባለበት አይቆይም ይላሉ፡፡ ዋጋው ተለዋዋጭ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአንዳንድ ምርቶችን የእለቱን ዋጋ አስመልክተው ነጋዴው እንዳሉት፤ አንድ ኪሎ የገንፎ እህል እንዲሁም በሶ 80 ብር፣ ስንዴ ለንፍሮ የሚሆነው በኪሎ 90 ብር፣ ለዳቦ የሚሆነው ደግሞ 65 ብር፣ ባቄላ የተከካ በኪሎ 80 ብር፣ አንድ ኪሎ ምስር 160 ብር፣ ድፍን ምስር 130 ብር፣ የአጃ ቅንጬ ከ90 እስከ 100 ብር፣ ጥቁር ገብስ ከ55 እስከ 60 ብር፣ ዱቄት ከ80 እስከ 85 ብር ነው፡፡

ነጋዴው አያይዘውም የክርስትና እምነት ተከታዮች ከሰሞኑ የሚያከብሩት የፋሲካ በዓልና የእስልምና እምነት ተከታዮች በአንድ ሳምንት ልዩነት የሚያከብሩት የረመዳን ጾም ፍቺ የሸቀጦች ፍላጎትን በእጥፍ እንዲጨምር እንደሚያደርገው ጠቅሰው፣ መንግሥት ገበያ የማረጋገት ሥራውን ከወዲሁ ቢሠራ መልካም ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

ለመጪዎቹ ሁለት በዓላት አስፈላጊና አይቀሬ ከሆኑ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች መካከል ዘይት አንዱ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ የሚመረት ጻሐይ ንጹሕ የኑግ ዘይትና ከውጭ አገር የሚገባውን የሱፍ ዘይት በሾላ ገበያ ስትሸጥ ያገኘናት ወጣት የማታ ብርሃኑ በበኩሏ የዋጋ ንረቱ የንግድ ሥራውን ቀዝቃዛ እንዲሆን አድርጎታል ትላለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ የአገር ውስጥ የኑግ ዘይት አምስት ሊትር 1200 ብር የሚሸጥ ሲሆን ከውጭ የሚገባው ደግሞ በ900 ብር እየተሸጠ ነው፡፡ ያም ቢሆን የሚገዛው ሰው በቁጥር ነው፡፡ እንደቀደመው ጊዜ ሰዎች ለበዓል የሚያደርጉትን አይነት እንቅስቃሴ እያደረጉ አይደለም የምትለው ወጣት የማታ፣ የዋጋ ንረቱ ለነጋዴውም ትልቅ ፈተና እንደሆነበት ታብራራለች፡፡

ነጋዴዎች ከአንድ ጀሪካን ዘይት አምስትና አስር ብር ብቻ ለማትረፍ እየሸጡ መሆናቸውን ጠቅሳ፣ ዘይት ዋጋው እጅግ ከመወደዱ የተነሳ ነጋዴውም አምጥቶ ለመሸጥ



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

ተቸግሯል ስትልም ነው ያመለከተችው። ከዚህ ቀደም 20 እና 30 ካርቶን የሚመጣበት ዋጋ ዛሬ አራትና ሶስት ካርቶን ብቻ እንደሚያመጣ ተናግራለች።

ከሌሎች የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች በተጨማሪ የፋሲካ በዓልን የሚያደምቀው ዶሮ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የዶሮ ገበያውንም ቃኘነው፡፡ ዶሮ በሾላ ገበያ ለአይን ሞልቶ እንደማይታይ፣በስፋት እየገባ እንዳልሆነ አስተያየት ከሰጡን ሸማቾችና ነጋዴዎች መረዳት ችለናል፡፡

በዶሮ ንግድ የተሠማራው አቶ ፍጹም ዘውዱ ወደ ገበያ እየገባ ያለው ዶሮ የፈረንጅ ነው ይላል፡፡ የፈረንጁ ዶሮም ቢሆን ዋጋው እንደ ፊቱ አይደለም ሲል ገልጾ፣ እሱም ውድ መሆኑን ይናገራል፡፡ ከዚህ ቀደም በጅምላ ሂሳብ ከሁለት መቶ ብር የበለጠ ዋጋ የማያወጣው የፈረንጅ ዶሮ አሁን ከ350 እስከ 400 ብር እየተሸጠ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ አሁን ያለው ዋጋም ለበዓሉ አንድ ቀን እስኪቀረው ድረስ በየሰዓቱ ሊጨምር ይችላል ሲል ስጋቱን ተናግሯል፡፡

‹‹የዋጋው መወደድ ለሸማቹም ሆነ ለነጋዴው ምንም ጥቅም የለውም፡፡ ነጋዴውም በስፋት አምጥቶ መሸጥ አያስችለውም፡፡ ሸማቹም እንደልቡ መግዛት አይችልም›› በማለት ለችግሩ ምክንያት ያላቸውን ጉዳዮች ጠቅሷል፡፡ በተለይ የሀበሻ ዶሮ በስፋት የሚመጣው ከአማራ ክልል ጎጃም አካባቢ እንደሆነ በመጥቀስ አሁን ላይ ከዚያ አካባቢ ምርቱ እየገባ አለመሆኑን ጠቁሟል፡፡

ከእነዚህ አስተያየቶች በመነሳት በአሁኑ ወቅት ሕዝቡን እየፈተነ ባለው የኑሮ ውድነት ላይ የበዓል ገበያው ተደርቦ ዋጋውን ይበልጥ እንዳያንረው በማድረግ በኩል ገበያ በማረጋጋት እየሠሩ ካሉ ተቋማት አንዱ ለሆነው የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጥያቄዎችን አቀረብን። መጪዎቹን ሁለት ታላላቅ በዓላት አስመልክቶ ገበያ በማረጋጋት ላይ ኮሚሽኑ ምን ዝግጅት አድርጓል ስንል የጠየቅናቸው የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወይዘሮ ጫልቱ ታምሩ በሰጡት ምላሽ፤ ኮሚሽኑ በአሁኑ ወቅት በዓላቱን መሠረት በማድረግ ገበያ ለማረጋጋት የተለያዩ ተግባሮችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ጫልቱ ገለጻ፤ የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ቀዳሚ ኃላፊነቱ ለሕዝብ አገልግሎት መስጠት ነው፤ ኮሚሽኑ በተለይም ገበያን በማረጋጋት ረገድ ሰፊ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

የሀገሪቱ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቁጥራቸው ውስን መሆኑን ኃላፊዋ ተናግረው፣ አብዛኛው የንግድ ሥራ በንግዱ ማኅበረሰብ መያዙን ነው የገለጹት፡፡ አስር በመቶ ያህል ድርሻ ያለው ኅብረት ሥራ የሀገሪቱን ገበያ በማረጋጋት ረገድ የበኩሉን እየተወጣ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የትንሳኤ በዓልን አስመልክቶ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ገበያ በማውጣት ማኅበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንዲችል በከተማዋ በአስሩም ክፍለ ከተሞች ተደራሽ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ምርቶቹ ለገበያ የቀረቡትም ከትናንት ማክሰኞ ጀምሮ ሲሆን፤ ይህም እስከ በዓሉ ዋዜማ ድረስ ይዘልቃል፡፡

ኮሚሽኑ ገበያን በማረጋጋት ልምድ እንዳለው የጠቀሱት ኃላፊዋ፣ በአሁኑ ወቅት የክልል ከተሞችን ሳይጨምር አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ 97 በሚደርሱ ቦታዎች ላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምርቶቻቸውን ይዘው እንዲቀርቡ አስችሏል ይላሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በሸማቾች የኅብረት ሥራ ደረጃ 138 ሸማች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተሰማርተዋል። በኦሮሚያ ዳር ዳር በተመሳሳይ 15 የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተሠማርተዋል፡፡ በጅሞ የገበያ ማዕከልም እንዲሁ 15 የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተለያዩ ምርቶችን ይዘው ወደ ገበያ ወጥተዋል። ማኅበረሰቡ ከትናንት ጀምሮ በየአካባቢው ወጥቶ ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንደሚችል ወይዘሮ ጫልቱ ጠቁመዋል፡፡

ኮሚሽኑ ገበያን ማረጋጋት ዋና ተግባሩ ነው፤ ለሕዝብ አገልግሎት የቆመ ተቋምም እንደመሆኑ በትክክል ገበያውን ማረጋጋት እንደሚችል ጠቅሰው፣ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለገበያ መቅረባቸውን ተናግረዋል። ለአብነትም የበቆሎና የስንዴ ዱቄትን ጨምሮ የተለያዩ ምርቶች ቀርበዋል፡፡ የስንዴ ዱቄት በኪሎ 47 ብር ሲሸጥ የበቆሎ ዱቄት ደግሞ በኪሎ 36 ብር እየተሸጠ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ጤፍ ከ5500 እስከ 6000 ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑንም ነው ያመለከቱት፡፡

በገበያው አትክልትና ፍራፍሬ መቅረቡን የገለጹት ወይዘሮ ጫልቱ፤ ሽንኩርት ከ25 እስከ 28 ብር በኪሎ እየተሸጠ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡ ዶሮና በግን ጨምሮ የእንስሳት ተዋፅዖ የሆኑ እንደ እንቁላልና ቅቤ ያሉትም በሁሉም ክፍለ ከተሞች መቅረባቸውን ጠቁመው፣ ሕዝቡ በየአካባቢው ወጥቶ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንደሚችል ነው ያስረዱት፡፡

ሁለቱን በዓላት ታሳቢ በማድረግ በቂ ምርት ወደ ገበያ ወጥቷል፡፡ ምርቶቹ በስፋት ከኦሮሚያ ክልል እንዲሁም ከደቡብ አካባቢ እየገቡ ይገኛሉ ያሉት የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ጠቁመዋል። አንዳንዶች ሆን ብለው ከፖለቲካ ጋር በማገናኘት ሰው ሠራሽ እጥረት እንዲፈጠር እየሠሩ እንደሆነም አስገንዝበው፣ ይህንን ችግር ለመፍታትም መንግሥት ከሕዝቡ ጋር በመሆን ለማስተካከል እየሠራ መሆኑንና ችግሩ በሂደት እንደሚፈታ አስረድተዋል፡፡

ለበዓላት ያስፈልጋሉ የተባሉ ምርቶች በሙሉ በኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት በአስሩም ክፍለ ከተሞች በተመጣጣኝ ዋጋ የቀረቡ መሆናቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ ጫልቱ፤ በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ይቀርብ የነበረው የእሁድ ገበያም ከሰኞ ጀምሮ ለተከታታይ ቀናት እንዲቆይ መደረጉም ገበያን ለሚረጋጋት ከተሠሩ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው ብለዋል፡፡

በሌላ የኢዜአ ዘገባ ለትንሳኤና ኢድ በዓላት የፍጆታ ምርቶች በሁሉም አካባቢ በቂ አቅርቦት መኖሩን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርም አስታውቋል፡፡ ከበዓላቱ አከባበር ጋር ተያይዞ በምርት አቅርቦት ዙሪያ የተደረገውን ዝግጅት በማስመልከት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ሰጥተዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ገብረመስቀል ጫላ፤ በተከታታይ ሳምንታት በሚከበሩት የትንሳኤ እና የኢድ አልፈጥር በዓላት የግብርና ምርቶችና የሸቀጦች አቅርቦት በስፋት መኖሩን አስታውቀዋል። በመሆኑም ላለፉት 20 ቀናት በክልሎች ከሚገኙ የንግድ ቢሮዎች አካላት ጋር በመነጋገር የምርት አቅርቦት በስፋት እንዲኖር መደረጉን ሚኒስትሩ ገልጸው፣ ኅብረተሰቡ በተረጋጋ መልኩ መሸመት እንደሚችል አስታውቀዋል።

በግብይት ሰንሰለቱ ውስጥ በመግባት የተለያዩ ሕገ-ወጥ ተግባራት ላይ የሚገኙ አካላት ካሉ በሕግ ተጠያቂ እንደሚደረጉም ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አብዲ ኡመድ፤ የግብርና ምርቶች፣ የእንስሳት ተዋፅዖና ሸቀጦች ጭምር በኅብረት ሥራ ማኅበራት በኩል በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረባቸውን ገልጸዋል። በአዲስ አበባ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሳያካትት ሌሎች 30 በሚጠጉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን የሚያቀርቡ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት የግብርና ምርቶችን፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ዱቄትና ሌሎችም ምርቶችን ለሸማቾች ማዘጋጀታቸውን ጠቅሰዋል። የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የእርድ እንስሳትን ጭምር ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆናቸውም ታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበዓላት ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የሚደረገውን የዋጋ ጫና ለመቀነስ ምርቶችን በብዛት ወደ ከተማ በማስገባት ላይ እንገኛለን ሲሉ መግለጻቸውን መገናኛ ብዙኃን መዘገባቸውን ጠቁመዋል።

በከተማችን የተጀመረው የሌማት ትሩፋት ንቅናቄ ለበዓሉ ዶሮ ለማቅረብ የሚያስችል አቅም እንድንፈጥር ረድቶናል ያሉት ከንቲባዋ፣ እነዚህ ጥረቶቻችንን በቀጣይ አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉም ገልጸዋል። የገቡት ምርቶች ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ሁሉም አካል ተባብሮ እንዲሠራ ለማሳሰብ እወዳለሁ ብለዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሞባይል ስልክ አጠቃቀም እና መዘዙ

**ቦጋለ አበበ**

ዘመናዊነት ካመጣቸው ችግሮች አንዱ ተፈላጊው መረጃ ሁሉ በስልካችን በኩል መምጣቱ እና ስልካችንን ለእርስ በርስ ግንኙነት፣ ለማኅበራዊ ሚዲያ፣ ለጌሞች እና ለመሳሰሉት ተጨማሪ ተግባራት ለረጅም ሰዓታት መጠቀም የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የሞባይል ስልክ መጠቀም ከጀመርን ከሁለት አስርተ ዓመታት እንኳን የበለጠ አይሆንም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን በተለይ በከተሜው አካባቢ ያለ ስልክ እስትንፋስ የሌለ እስከመምሰል ደርሷል፡፡

ዋናው ጥያቄ የሞባይል ስልኮችን መጠቀም ሳይሆን አጠቃቀሙ ላይ ያለው ግንዛቤ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የብዙዎቻችን አጠቃቀም በሳይንስ ያልተደገፈና በዘፈቀደ መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ አስገራሚው ነገር ግን አጠቃቀማችን ቴክኖሎጂው በተለይም በጤና ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ችግር በቀላል ሳይንስ ማስቀረት እየቻልን ቸልተኛ መሆናችን ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል በመኝታ ሰዓት ሞባይል ስልኮችን መጠቀም ከስክሪኑ የሚወጣው ጨረር አዕምሮን እንዲጨናነቅና እንዲነቃ ስለሚያደርገው ለእንቅልፍ እጦት ይዳርጋል። ከዚህ አንጻርም ከመኝታ ከአንድ ሰዓት በፊት ከእጅ ስልክ ጋር ብንለያይ ሳይንስ ይመከራል። እኛ ጋር ግን ይህ ተቃራኒ ነው፡፡ እንዲያውም እንቅልፍ እንቢ ሲለን በቀጥታ ስልክ መነካካት ነው የሚቀናን፡፡

ይህ የሞባይል ስልክ አጠቃቀም ችግር ከኛም አልፎ መዘዙ ለሕፃናት መትረፉን ልብ ልንለው ይገባል፡፡ በየቤቱ ሕፃናት ለረዥም ጊዜ የሞባይል ስልክ ሲጠቀሙ ማየት አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ይህን እንደ ችግር የምንቆጥረውም አይደለም፡፡ በእርግጥ መቼና በየትኛው ዕድሜ ለልጆች ስልክ ይሰጥ የሚለው 'የሚሊዮን ዶላር' ጥያቄ ነው። አንዱ ወገን ልጆች ዘመናቸውን መምሰል ነው ያለባቸው፣ መረጃ የሚቃርሙት በስልክ ነው፣ ስለዚህ መነካካት እስከቻሉ ድረስ ይጠቀሙ፤ ይበርብሩ ይላል። ሌላኛው 'የለም፤ የለም፤ አደጋው ይከፋል፣ መርገምቱ ይሰፋል' ይላል። ክርክሩን ለጊዜው ወደ ጎን ትተነው ከጤና አኳያ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን በቀላል ሳይንስ ማስቀረት እየቻልን ቸልተኛ የሆንባቸውን ጥቂት ነገሮች በጥናቶች አስደግፈን እንታዘብ፡፡

ጥናቶች እንዳሳዩት የሞባይል ስልክን አዘውትረው የሚጠቀሙ ሕፃናት እስከ 3% የሚደርስ ከዕድሜ እኩዮቻቸው ተጨማሪ ለአጭር ዕይታ (short sidededness) ሕመም የመጋለጥ ዕድል አላቸው። ከእይታቸውም ባለፈ የእንቅልፍ መዛባት፣ የመደበት፣ የራስ ምታት፣ የአንገት ሕመም እና ከፍ ሲልም እንደ ኦቲዝም ባሉ የዕድገት እክሎች የመጠቃት ዕጣ ሊገጥማቸው ይችላል።

ሌላው ለረጅም ሰዓት ስልክ እየነካኩ መቆየት ከሚያመጣቸው ችግሮች ውስጥ ምስሉ ላይ በሚታየው መልኩ አንገትን ጎንበስ አድርጎ ዘለግ ላለ ጊዜ ከመቆየት ጋር የተያያዙ የአንገት ዲስኮች ማበጥ፣ የአንገት ጡንቻዎች አቅም መዛነፍ እና ለረጅም ጊዜ ጫና የሚበዛበት የፊተኛው የአንገት ክፍል ላይ ያሉ የአጥንት ጠርዞች በጫና ምክንያት ያለዕድሜ መበላት (degeneration) ይጨምራል። ይህም ኑሮን ለሚያውክ የአንገት ሕመም እና ለአላስፈላጊ ቀዶ ሕክምና ይዳርጋል። ይህ በሳይንስ የተደገፈ የሞባይል ስልክ መዘዝ መፍትሔው ቀላል ቢሆንም ብዙዎች ከቁብ አንቆጥረውም፡፡

ለምሳሌ ሳይንስ እንደመፍትሔ ከሚያስቀምጣቸው ነጥቦች መካከል በአጠቃላይ ሞባይል የምንጠቀምበትን ሰዓት በየመሐሉ እረፍት ያለበት እና ያልተራዘመ እንዲሆን ማስቻል አንዱ ነው፡፡ ግን ስንቶቻችን ይህን ተገንዝበን ተግባራዊ እናደርጋለን የሚለው የሁላችንም ጥያቄ ነው፡፡

ሕፃናት ለአይናቸው በሚኖረው ቅርበት ምክንያት ከነአካቴው በሞባይል ስልክ ጌም ባይጫወቱ ይመከራል። የግድ መጠቀም ካለባቸውም ትንሽ የጥንቃቄ ርምጃ ብንወስድ ከትልቅ ችግር ልንታደጋቸው እንችላለን። ለምሳሌ ያህል የብርሃኑን መጠን መቀነስ፣ የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ጨረሩን ጫና ለመቅረፍ የኔትወርክ ግንኙነት ("ኮኔክሽን") የሌለው ስልክ/ታብሌት መስጠት አልያም "ኤር ፕሌን ሞድ" ላይ ማድረግ አንዱ አማራጭ ሊሆን ይችላል። በፕሮግራም እንዲጠቀሙ ማድረግ እና ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ እንዲጠቀሙ በፍፁም ባለመፍቀድ ባሕሪውን እንዲያዳብሩት ማድረግም ከባድ አይደለም።

ማንኛውም ዕድሜ ላይ ያለን ሰዎች የሥራችን ባሕሪ ለረጅም ሰዓታት ስልክ መነካካት የሚያስገድደን ከሆነ ቢያንስ ምስሉ ላይ የሚታየውን "የቴክስት ፖዚሽን" የሚል ስያሜ የወጣለትን አይነት አንገትን ጎንበስ በማድረግ ለተራዘመ ሰዓት መነካካት ወይም "ቴክስት መፃፍ/ ቻት ማድረግ" የሚያመጣውን ችግር በመገንዘብ ከአንገታችን ቀና ብለን ለመጠቀም መሞከር ፣ በየመሐሉም እንቅስቃሴ ማድረጊያ ዕረፍት መውሰድ ያስፈልጋል። ግን ለነዚህ ቀላል መፍትሔዎች ስንቶች ግንዛቤው ኖሯቸው ተግባራዊ ያደርጉታል የሚለው ጉዳይ አሳሳቢ ነው፡፡

የሞባይል ስልክ ጉዳይ ሲነሳ በዚህ ዘመን የማኅበራዊ ሚዲያዎችን በጎና መጥፎ ገፅታ በጥቂቱም ቢሆን ሳይጠቅሱ ማለፍ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ስልክ በመነካካት ረጅም ሰዓት እንድንወስድ ከሚያደርጉት ዋነኛ ምክንያቶች ግንባር ቀደሞቹ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ናቸው፡፡ ለዛሬው ከማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በተለይም ልጆች በየትኛው ዕድሜ ላይ ምን ይሰማቸዋል በሚል በተደረገ አንድ ሰፊ ዓለም አቀፍ ጥናት ያስቀመጠውን እንመልከት፡፡ ጥናቱ 17ሺ የሚሆኑ አዳጊዎች እና ወጣቶች (ዕድሜያቸው ከ10 - 21 የሆኑ) ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በውጤቱም ሴቶች ከ11 - 13 ወንዶች ደግሞ ከ14 - 15 ዓመት ያሉት በተለይ ማኅበራዊ ሚዲያን መጠቀም በጀመሩ በዓመቱ ከፍተኛ እርካታ የማጣት ስሜት ተስተውሎባቸዋል። የሚገርመው ደግሞ ስልክና ማኅበራዊ ሚዲያ ባልተጠቀሙት ላይ የእርካታና እፎይታ ስሜት መታየቱ ነው።

በአሥራዎቹ የሚገኙ አዳጊዎች ሁልጊዜም ቢሆን ሌላው ስለነርሱ ምን እንደሚያስብ ያስጨንቃቸዋል። ማኅበራዊ ሚዲያ ደግሞ ሰዎች በግላጭ ፍቅርና ጥላቻቸውን የሚረጩበት መድረክ ነው። አዳጊዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተጽዕኖ ውስጥ የሚወድቁትም ለዚሁ ነው። እርካታ ጥሏቸው ይበናል። ለምን ቢባል ሁሌም የሆነ የሚበልጣቸው እኩያቸው በማኅበራዊ ሚዲያ አለ። ያ ደግሞ ደስታቸውን ይቀማቸዋል። ይህ ደግሞ በቤተሰብ ብቻ ሳይሆን እንደ ማኅበረሰብም ይዞ የሚመጣው መዘዝ ከባድ ነውና እናስብበት፡፡

# ዓለም አቀፍ



## ደቡብ ኮሪያ ለዩክሬን የጦር መሣሪያ ለመላክ ማመንታቷን ከአሜሪካ ሾልኮ የወጣ መረጃ አሳየ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከአሜሪካው ፔንታጎን ሾልከው የወጡ ሰነዶች በደቡብ ኮሪያ ከፍተኛ ባለሥልጣናት መካከል ለዩክሬን የጦር መሣሪያ መላክን በተመለከተ ስለነበረው ውይይት ይፋ አደረገ።

ምስጢራዊ ሰነዱ አሜሪካ ለአስርተ ዓመታት አጋር ወይም ወዳጅ የምትላትን ደቡብ ኮሪያን ስትሰልል እንደነበረም ፍንጭ የሰጠ ነው። ስለ ዩክሬኑ ጦርነት፣ የአሜሪካ አጋሮች እንዲሁም ቻይናንም በተመለከተ ሰነዱ መረጃዎችን አካቷል።

ሾልኮ የወጣው ይህ መረጃ ደቡብ ኮሪያ ከአሜሪካ እና ከሩሲያ ጋር ያላትን ግንኙነት ሊያበላሽ የሚችል አቅም እንዳለውም ተጠቅሷል።

ደቡብ ኮሪያ የወጣውን መረጃ እየመረመርኩ ነው ብትልም በፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤቷ ውስጥ የሚደረጉ ግላዊ ንግግሮችን ለመጥለፍ እንደማይቻል አስታውቃለች። ሆኖም የተባለው ውይይት ከምድር በታች ባለው ጽሕፈት ቤቱ ውስጥ የተካሄደ ሊሆን አይችልምም ብላለች።

ዋሽንግተን ይህንን መረጃ ያሾለከውን አካል ለማጣራት እየጣረ መሆኑን አስታውቆ፤ ፔንታጎን በበኩሉ መረጃው ለሀገር ደኅንነት ከፍተኛ አደጋን ጋርጧል ብሏል። ቢቢሲ የተመለከተው ይህ ሰነድ ደቡብ ኮሪያ ለዩክሬን የጦር መሣሪያ ለመሸጥ ማመንታት ውስጥ መግባቷን የሚያሳይ ነው።

አሜሪካ ዩክሬንን ለማስታጠቅ ደቡብ ኮሪያን ስትገፋ የቆየች ሲሆን ነገር ግን በጦርነት ላይ ላሉ አገራት የጦር መሣሪያ አቅርቦት የማያሰጠውን ፖሊሲዋን በመጥቀስም ስትቃወም ቆይታለች።

ባለፈው ዓመት ደቡብ ኮሪያ በዩክሬን ጦርነት ምክንያት የተሟጠጠውን የጦር መሣሪያ ክምችቷን ለመሙላት የከባድ መሳሪያ መተኮሻዎችን ለአሜሪካ ለመሸጥ ተስማምታ ነበር።

ሆኖም እነዚህን መተኮሻዎች አሜሪካ ለዩክሬን እንዳትሰጥና ለራሷም እንድትይዘው ደቡብ ኮሪያ የስምምነቱ አካል እንዲሆን አጽንኦት ሰጥታለች። ሾልኮ የወጣው ሰነድ እንደሚያሳየው የደቡብ ኮሪያ መንግሥት ስምምነቱ እንዳሳሰበው እና አሜሪካ እነዚህን የጦር መሣሪያዎች ለዩክሬን አሳልፋ ልትሸጥ እንደምትችልም መጠርጠሩን ያሳያል።

ሰነዱ በሁለቱ የደቡብ ኮሪያ ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዮል ከፍተኛ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪዎች መካከል ለአንድ ወር ያህል የተደረገውን ምስጢራዊ ውይይት በዝርዝር ያካተተ ነው።

## አውሮፓ ከአሜሪካ ተጽዕኖ ልትላቀቅ እንደሚገባ ፕሬዚዳንት ማክሮን ተናገሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አውሮፓ ከአሜሪካ ተጽዕኖ ልትላቀቅ እንደሚገባ ፕሬዚዳንት ማክሮን ተናገሩ፡፡ አውሮፓ ሦስተኛ የዓለም አማራጭ የመሆን እድሏን ልትጠቀም እንደሚገባ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል፡፡

የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን እና የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን ኡርሱላ ቮንደረሊን ወደ ቻይና አቅንተው ከፕሬዚዳንት ሺ ጅምፒንግ ጋር መምከራቸው ይታወሳል፡፡

ፕሬዚዳንት ማክሮን የቤጂንግ ቆይታቸውን አጠናቀው ወደ ሀገራቸው እየተመለሱ ባሉበት አውሮፕላን ውስጥ የነበረው የፖለቲካ ጋዜጠኛ ቃለመጠይቅ አድርጎላቸው እንደነበር ተገልጿል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በዚህ ጊዜ እንዳሉት አውሮፓ በአሜሪካ ላይ ጥገኛ መሆኗን ያመኑ ሲሆን ይህ ግን ትክክል አለመሆኑን እና ሊስተካከል ይገባል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል፡፡

የአውሮፓ ኃይል አቅርቦት፣ የጦር መሣሪያ ቴክኖሎጂ፣ የዓለም ንግድ እና ሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ በአሜሪካ የበላይነት የተያዙ መሆናቸውን በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አክለውም አውሮፓ የአሜሪካ እና ቻይና ኃይል ሚዛን ማስጠበቂያ ሊሆኑ አይገባም ያሉ ሲሆን አውሮፓ በራሷ ልትቆም እንደሚገባ ተናግረዋል ተብሏል፡፡

የዓለም መሪነትን ዋሽንግተን እና ቻይና ቢቆጣጠሩም አውሮፓ ሦስተኛዋ ባለ ተጽዕኖ እንድትሆን ብራስልስ ቤጂንግን እንደ ስጋትነት ሳይሆን እንደ አጋር ማየት የሚያስፈልግበት ወቅት መሆኑንም



ፕሬዚዳንቱ መናገራቸው በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡

አውሮፓ ያጋጠማትን ጦርነት በራሷ መፍታት የምትችልበት አቅም እንደሌላት ፕሬዚዳንት ሺ ፒንግ ቤጂንግን ለጎበኙት ፕሬዚዳንት ማክሮን እና ቮንደርሊን እንደተናገሩ እንዲሁም የታይዋን ጉዳይ የቻይና የውስጥ ጉዳይ መሆኑን በአንክሮ መናገራቸም ተገልጿል፡፡

ዋሽንግተን በተለይም ቻይናን፣ ሩሲያን እና ኢራንን ለመጉዳት በሚል ማዕቀብ መጣሏ የአውሮፓን ንግድ በአሜሪካ ላይ ብቻ እንዲመሠረት እና በማዕቀቦቹ የአውሮፓ ኩባንያዎችም ሁለተኛ ተጎጂ እንዲሆን አድርጓል ብለዋል ተብሏል ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የሕይወቷን ጨለማ በፅናት አልፋ ለሌሎች ፅናት የሆነች እንስት

ማህሌት አብዱል

‹

‹ለምንኖርባት ዓለም ኪራይ መክፈል አለብን›› በሚለው ንግግራቸው ይታወቃሉ፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በባህር ማዶ ለተጎዱ፤ ግራ ለገባቸው ፣ ጭልም ድንግዝግዝ ላለባቸው የብርታት፤ የጥንካሬ የተስፋ ምሳሌ ተደርጋ ትጠቀሳለች፤ የዛሬዋ የባለውለታ አምዳችን ባለታሪክ፡፡

በተለይም ደግሞ በባሎቻቸው ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ህይወት በመታደግና ለተቸገሩ ፈጥኖ በመድረስ ዝናዋ ከኢትዮጵያ ጣሊያን ብሎም አሜሪካ ድረስ የናኘ ብርቱ ኢትዮጵያዊ ሴት ናት፡፡ በአሜሪካ ምድር መንገድ የወደቁ ኢትዮጵያውያንን በመሰብሰብና የችግራቸውን ጊዜ እንዲሻገሩ በማድረጓም ‹‹የከፉ ቀን ደጀን›› የሚል ስያሜ አግኝታለች፡፡ ወ/ሮ መንበረ አክሊሉ፡፡

ትውልዷም ሆነ እድገቷ ጎጃም፣ ደብረማርቆስ ነው። ለእናቷ የመጨረሻ ልጅ የሆነች ይህች ሴት ወላጅ አባቷን ግን ጨርሶ እንዳማታውቃቸው ትናገራለች። ትምህርት ያልቀመሱ እናቷ ከሻይ ቤት ጀምረው ባሳደጉት ሆቴላቸው ገቢ ነው አባትም እናትም ሆነው እሷንም ሆነ ወንድም እህቶቿን ለብቻቸው ማሳደጋቸውን ትገልፃለች፡፡

የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ የሆነው ይሄው የሆቴል ንግድ ታዲያ የኋላ ኋላ ወላጅ እናቷን እንዳሳጣት ዶክተር መንበረ ትናገራለች። ልጆቻቸውን ለወግ ማዕረግ ለማብቃት እድሜያቸውን ሁሉ ዋጋ ሲከፍሉ የኖሩት እኚሁ እናት በአንዲት በተረገመች የስቅለት ምሽት አንድ ሻምበል ከሌላ ደንበኛ ጋር በተፈጠረ አምባጓሮ የተተኮሰች ጥይት ሰለባ ህይወታቸውን አጡ። ከሁሉ የሚያስከፋው ይሄ ሁሉ አሳዛኝ ትእይንት ሲከናወን የአስር አመቷ ህፃን መንበረ በአይኗ በብረቱ የተመለከተች መሆኑ ነው። ይህ ሰቅጣጭ ግድያ ታዲያ መቼም ለልጅ አይደለም ለአዋቂም ቢሆን ይህ ምንያህል ከባድ እንደሆነ ነጋሪ አያሻውም። እናም የባለታሪካችን ሌላኛውን የህይወት ምዕራፍ አሀዱ ብላ የጀመረችውም ያኔ ነበር፡፡ ከእናቷ ሞት በኋላ እንደማንኛውም ወላጆቹን እንዳጣ ህፃን ፆታዊ ጥቃትን ጨምሮ ብዙ ችግሮችን ለመጋፈጥ ተገደደች፡፡

እንግዳችን ወ/ሮ መንበረ የእናቷን ህልፈት ተከትሎ እሷን የማሳደጉና መንከባከቡ በታላቅ እህቷ እጅ ላይ አረፈ፡፡ እናም በደብረማርቆስ ንጉስ ተክለሀይማኖት ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ተከታተለች። በቀጣይም በወቅቱ አዲስ አበባ ኗሪ የነበረው ወንድሟ ዘንድ ተጠግታ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቀቀች።

ከፍተኛ የሆነ የጥበብ ፍቅር ስለነበራትም የቲያትሩን ዓለም ለመቀላቀል ሻተች፤ ሆኖም ታላቅ ወንድሟ ‹‹አንቺ የፋንታዬ ተገኝ ልጅ ነሽ፤ አዝማሪ ተብለሽ እንድታድጊ አልፈልግም›› የሚል መከላከያ በማቅረብ ጫና አሳደረባት፡፡ ይሁንና የወንድሟን ሃሳብ ‹‹አሻፈረኝ›› ብላ ወደምትወደው ሙያ ዘው ብላ ገባች፤ ለዚህም መንደርደሪያ ይሆናት ዘንድ በብዙ ልፋትና ድካም የትወና ሙያ ማሰልጠኛ ውስጥ ትምህርት ጀመረች። እናም ራስ ቲያትር፤ ሀገር ፍቅር፤ ብሔራዊ ቲያትር ቤቶች መድረክ ላይ በመሳተፍ ተዋናይ የመሆን ህልሟን እውን ማድረግ ቻለች።

የፍቅር ህይወቷም በዚህ ወቅት ነበር የተጠነሰሰው፤ የመድረክና የሙያ አጋሯ ከሆነው ሰው ጋር ተወዳጀች፤ ይሁንና የፍቅር ግንኙነታቸው እንደመጀመሪያው በአድናቆት፤ በሙገሳ አልዘለቀም፡፡ ይልቁኑም ዕለት ዕለት በአካላዊም ሆነ በስነ-ልቦናዊ ጥቃት የታጀበ ሆነ። የፍቅር አጋሯ የነበረው ነፃ የትምህርት እድል ወደ ጣሊያን ተጓዘ፡፡ ወጣቷ ተዋናይም የፍቅር አጋርዋ ያለበትን አጉል ባህሪ ‹‹እተዋለሁ›› ያለውን ቃል በማመን እና ሙያውንም ለማሳደግ ስትል ተከተለችው፡፡

ጣሊያን ሀገር ግን የጠበቀችው የትወና ሙያ ስኬት ሳይሆን አስቸጋሪ የትዳር ህይወት ሆነ። ትዳር የተቀደሰ ግንኙነት፤ ቤተሰብም የተከበረ ነው በሚል ለትዳሯ ቅድሚያ ለመስጠት ወስና የህይወትን መራራ ጎን ተጋፈጠች፡፡ ይሁንና ትዳር እንዳሰበችው የምታርፈበት ከመሆን ይልቅ የእሳት ወላፈን ሆኖ መልሶ ይለበልባት ጀመር፡፡

በተለይም የትዳር አጋሯ ምሎ ፤ተገዝቶ የነበረውን ክፉ ባህሪውን ሊተው ባለመቻሉ የጣሊያን ቆይታዋ ከፊቱ የባሰ ከባድ አደረገባት፡፡ የሰላም ቀናቶቿም ብዙ ቀናት መዝለቅ ባለመቻላቸው ኑሮዋን እንድትጠላ አደረጋት፡፡ ሀገር ቤት ሳለ ያደርግ እንደነበረው ዘወትር በውሃ ቀጠነ ሰበብ እየደበደበና እያስለቀሰ፤ ከፊትና ከኋላ በሲጋራ እያቃጠለ፤ ብሎም ወሲባዊ ጥቃቶችን ያደርስባት ቀጠለ፡፡ ይህም ስቃይ ውስጥ ከተታት፡፡ ይህ አልበቃ ብሎት ‹‹ለመጨረሻ ጊዜ አብረን በሰላም እንድንኖር የምትፈልጊ ከሆነ ለእኔ ያለሽን ፍቅር ለማረጋገጥ ስትይ የፊት ሁለት ጥርሶችሽን በገዛ እጆችሽ አውልቀሽ ጠብቂኝ›› የሚል ለአዕምሮ የሚከብድ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡

የዛሬዋ ባለታሪካችን ዶክተር መንበረ ይህ ቃል የማንቂያ ደውል ነው የሆነላት፡፡ ለሀገሩ ባይተዋር መጠጊያ አልባ መሆንዋ ሳያግዳት ‹‹ጨርቄን ማቄን›› ሳትል ለመውለድ ስድስት ቀናት ብቻ እየቀራት ብን ብላ ቤቱን ለቃለት ወጣች፡፡ እናም በሰው ሀገር ማረፊያዋ ቤተክርስቲያን ደጅ ሆነ፡፡ ሁሉ ሆድ የሚያባባውን ልቅሶዋን የተመለከቱት አባት ቀርበው አነጋገሯት፤ ችግሯንም ተረድተው በማዘር ትሬዛ በተከፈተ የሴቶች መጠለያ ውስጥ እንድትገባ አደረጉ፡፡ ከስድስት ቀናት በኋላም ከበርካታ የመንገድ ተዳዳሪዎች፤ የአዕምሮ ህመምተኞች መካከል ልጇን በሰላም ተገላገለች፡፡ ይሁንና የአራስ ወግ የማየት ለእሷ የቅንጦት ቅንጦት ነበር፡፡

ከወለደችበት ዕለት ጀምሮ ከዚህ ለመኖር አስቸጋሪ ከሆነው ሥፍራ ልጇን ማስወጣት የእለት ተእለት ሃሳቧ ነበር፡፡ ለሁለት ወራት ያህል በመጠለያው ከቆዩ በኋላ በአካልም በመንፈስም ታድሳ ነበርና ልጇንም ሆነ ራሷን ማቋቋም አላቃታትም። ልጇም ነፍስ እስኪያውቅ ድረስ በጣሊያን የሰው ቤት ሰራተኛነት ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች እየሰራች ክርስቲያን የተባለ ወንድ ልጇን ለማሳደግና ለማስተማር በቃች።

ክርስቲያን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ሲጨርስ የጣሊያንን ምድር ለቃ ወደ አሜሪካ ተጓዘች። አሜሪካ ከነልጇ ከገባች በኋላም የጣሊያንኛ ቋንቋ ችሎታዋን በመጠቀም አንድ የጣሊያን ሬስቶራንት ውስጥ እንግዳ ተቀባይነት ተቀጥራ እስከ ሬስቶራንት ስራ አስኪያጅነት ደረሰች፡፡ ይሁንና ትሰራበት የነበረው ሆቴል በኪሳራ ምክንያት ለሽያጭ ሲቀርብ ግራ ተጋብታ ተቀምጣ ሳለ ለዓመታት ጠንካራ ሰራተኝነቷን ያስተዋለው አንድ ጣሊያናዊ ደንበኛቸው “ገንዘብ ላበድርሽና ሰርተሽ ክፈይኝ” የሚል ጥያቄ አቀረበላት፡፡ መንበረም ይህንን ከፈጣሪ የተላከ መልካም እድል ያለአንዳች ማወላወል ነበር የተቀበለችው፡፡ ጠንክራ በመሥራት ከጣሊያኑ ሰው ያገኘችውን ብድርም በጣም በአጭር ጊዜ መመለስ ቻለች። አሁን ላይ ወ/ሮ መንበረ አክሊሉ የሳሉቴ ቪታ ሬስቶራንት ባለቤት ከመሆንም ባለፈ ለበርካታ ሰዎች የስራ እድል በመፍጠርም በሀገሩ መንግስት እውቅና ተችራለች፡፡



ወ/ሮ መንበረ አክሊሉ፤

**‹‹ለመጨረሻ ጊዜ አብረን በሰላም እንድንኖር የምትፈልጊ ከሆነ ለእኔ ያለሽን ፍቅር ለማረጋገጥ ስትይ የፊት ሁለት ጥርሶችሽን በገዛ እጆችሽ አውልቀሽ ጠብቂኝ›› የሚል ለአዕምሮ የሚከብድ ትዕዛዝ አስተላለፈ**

የብርቱዋ መንበረ ሌላኛው የህይወት ገፅታዋ ደግሞ እንደእሷ በአስቸጋሪ ሕይወት ምክንያት ለስደት የተዳረጉ፣ ሀገር እስከ መርዳት የደረሰ ከፍታዋ ነበር። የትናንትና ህይወቷና ቁስሏ ለዛሬ ብርታት ሆኗት ዛሬ ለሌሎች የምትተርፍ ሆናለች፡፡ ብሎም ከእናቷ የወረሰችውን ጥንካሬና ለሁሉ ደራሽነት በማስቀጠል የብዙዎቹን ህይወት ለመታደግ ችላለች፡፡

ህይወት በብዙ መልኩ የፈተነቻት ወ/ሮ መንበረ በመከራዎች ውስጥ እንድታሸንፍ የረዷትን ሰዎች በማሰብ አሁን ለዓለም መልሳ እየሰጠች ትገኛለች። በምትኖርበት አሜሪካ አቅመ ደካማ ሴቶችን፣ ቤት አልባዎችን፤ ደጋፊ የሌላቸውን ህፃናትንና አረጋውያንን ታግዛለች፤ ትረዳለች፤ በየወሩም ሆቴሏን ለምገባ ታውላለች፡፡

በተለይም በየዓመቱ አሜሪካውያኑ የሚያከብሩትን የምስጋና ቀን ምክንያት በማድረግ እስከ አንድ ሺ የሚሆኑ ችግረኞችን በሬስቶራንቷ ትጋብዛለች፡፡ በተመሳሳይ በሴቶች ቀን ቤት አልባ ሴቶችን ሰብስባ ቀኑን በደስታ እንዲያሳልፉ ታደርጋለች፡፡ በተጨማሪም በአካባቢዋ ያሉ ወጣቶች በማገዝ ለብዙዎች አርአያ የሚሆን ተግባር ፈፅማለች፡፡

ከዚህም ባሻገርም ተወልዳ ባደገችበት በደብረማርቆስ ከተማ በእናቷ ፋንታዬ ስም የተሰየመ የሴቶች መጠለያ በመመስረት ከ80 የሚልቁ ወላጅ አልባ የሆኑ፤ የትምህርት እድልን ላላገኙ፤ አካል ጉዳተኞች የሆኑ ልጃገረዶች ከፍተኛ የትምህርት እድልን እንዲያገኙ በማድረግ እያበቃች ትገኛለች። በተጨማሪም ለደብረማርቆስ ለህፃናት ማሳደጊያ የሚሆን የሶስት ሚሊዮን ብር ቤት ገዝታ አስረክባለች። እንዲሁም ከአመታት በፊት በባሏ አሲድ የተደፋባትን አንዲት ሴት አሜሪካ በመውሰድ በማሳከም ህይወቷን ለማትረፍ ባደረገች ጥረት አለም አቀፍ እውቅና አግኝታለች።

በዚህ ብቻ ግን አልተወሰነችም፤ ብዙ አመታት ያሳለፈችበት ጣሊያን በኮሮና ቫይረስ ህዝቧ ሲረግፉባት ዝም ብላ ማየት ስለተሳናት 27ሺ ዶላር በመርዳት መልሳ አለምን አስደምማለች። በቅርቡ ደግሞ በጦርነቱ ምክንያት ለተፈናቀሉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቿ የ50 ሺ ዶላር ድጋፍ በማድረግ የብዙ መገናኛ ብዙኃንን ቀልብ መሳብ ችላለች፡፡

ዶክተር መንበረ አክሊሉ በእነዚህና ዘር ቀለም ሳትመርጥ ባደረገቻቸው በሌሎች በጎ ምግባሮቿ በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ያገኘች ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል በአሜሪካ ባደረገችው ማህበራዊ ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት እውቅና፣ ምስጋና፣ ሽልማቶች ተሰጥቷታል፡፡

ኦክላንድ ሆሊኔልስ ዩኒቨርሲቲ እና ከቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬትን አግኝታለች፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ ደረጃ በክብር የሚታወቅ ጃፈርሰን አዋርድ ተሸላሚ ሆናለች፡፡ እንዲሁም በ2014 ዓ.ም ከካሊፎርኒያው ሆሊኔምስ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ማዕረግ የተሰጣት ሲሆን፤ የወቅቱ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ዊሊያም ሄንስ የዶክተር መንበርን ታሪክ “ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም” በሚል ሰዎች የበኩላቸውን ጥረት ካደረጉ የማይፈታ ችግር እንደሌለ ጥሩ ማሳያ እንደሆነች አድርገው አቅርበው ነበር፡፡

የሀገር ቤቱ የአድዋ የባህልና የታሪክ ህብረት የዶክተር መንበረን መልካምና በጎ ምግባሯን፤ ሰፊ ልቧን ፤ እናትነቷን ፤ ለጋስነት እና ደግነቷን በመመልከት በሰባተኛው ዙር የአርአያ ሰው ሽልማት መታሰቢያ አድርጎ በመምረጥ ሸልሟታል፡፡

እኛም መገፋቷንም ሆነ በህይወቷ ያጋጠሟትን ክፉ ነገሮች ወደ መልካም በመቀየር ከራሷ አልፋ ለሌሎች መትረፍ የቻለችው፤ ከተወለደችበት ቀዬ ጀምሮ ስደተኝነቷን ሳይንቁ እስከተቀበሏት ኃያላን ሀገራት የደጎች አብነት አድርገናታል፡፡

የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በዶሃ ዳይመንድ ሊግ የወንዶች 3ሺ ሜትር ፉክክር በጉጉት ይጠበቃል

**ብርሃን ፈይሳ**

በ14 የዓለም ከተሞች የሚካሄደው ዓመታዊው የዳይመንድ ሊግ ውድድር ከሳምንታት በኋላ በኳታሯ ዶሃ ይጀመራል። ውድድሩን ተከትሎም በስፖርት ቤተሰቡ ትኩረቱን በ3ሺ ሜትር ርቀት ላይ አድርጓል። አምስቱ የወቅቱ ድንቅ ብቃት ባለቤት የሆኑ አትሌቶች በዚህ ውድድር ላይ እንደሚካፈሉ ማረጋገጣቸው ደግሞ ይበልጥ ፉክክሩን አጓጊ አድርጎታል። በተለያዩ ውድድሮች ባስመሰከሩት ጥንካሬ ለአሸናፊነት ከፊት ረድፍ ከተቀመጡትና በውድድሩም ለአሸናፊነት ተጠባቂ ከሆኑት አትሌቶች መካከል ሶስት የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ናቸው።

በዶሃ ከሚካሄዱ ፉክክሮች መካከል በተለይ በ3ሺ ሜትር የሚካሄደው ፍልሚያ ከፍተኛ ትኩረት ከወዲሁ ያገኘውም የርቀቱን ባለ ክብረወሰን አትሌት ከሌሎች በርቀቱ ታዋቂ የሆኑ አትሌቶች ጋር ስለሚያገናኝ ነው። በተለይም ወጣቱ ድንቅ አትሌት በርቀቱ ከፍተኛ ልምድ ካካበተው ሞሮኳዊ አትሌት የሚኖራቸው ፉክክር ተጠባቂ ሲሆን፤ በርቀቱ የተሻለው አትሌት የሚለይበትም ይሆናል። ከሁለት ወር በፊት በሌቪን የ3ሺ ሜትር ርቀት የዓለም ክብረወሰንን በመስበር የግሉ ያደረገው ወጣቱ አትሌት ለሜቻ ግርማ ከተጠባቂዎቹ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አንዱ ነው። ከአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና አንስቶ በአጭር ጊዜ እስከ ትልልቅ የውድድር መድረኮች ስኬታማ መሆን የቻለው ለሜቻ የቅርብ ጊዜ ድሉን ይደግማል የሚል ከፍተኛ ግምት አግኝቷል።

የሁለት ጊዜ የዓለም ሻምፒዮና እንዲሁም የቶኪዮ ኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያ ባለቤት የሆነው ለሜቻ፤ ባለፈው ዓመት በተካሄደው የቤልግሬድ የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮናም የብር ሜዳሊያ ማጥለቁ የሚታወስ ነው። በተያዘው የውድድር ዓመት ደግሞ በዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና ተሳትፎው ሌቪን ላይ 3ሺ ሜትር ርቀትን 7:23.81 በሆነ ሰዓት የዓለም የክብረወሰን ባለቤት መሆን ችሏል። ይህም የ22 ዓመቱን አትሌት በርቀቱ ቅድሚያ ተጠባቂ ሲያደርገው ዶሃ ላይም እንደተለመደው ብቃቱን በማስመስከር አሸናፊ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል። ይሁንና ፈታኝ ፉክክር እንደሚገጥመው ግልጽ ነው።



በዶሃ ዳይመንድ ሊግ የ3ሺ ሜትር ፉክክር በጉጉት ይጠበቃል፣

ምክንያቱም ተፎካካሪው ለረጅም ዓመታት 3ሺ ሜትር መሰናክልን የሮጠውና በቶኪዮ ኦሊምፒክ እንዲሁም በዩጂኑ የዓለም ሻምፒዮና ለሜቻን የረታው ሞሮኳዊው አትሌት ሶፊያን ኤል ባካሊ በመሆኑ ነው። አትሌቱ በተለይ የሚታወቀው በመሰናክል ይሁን እንጂ በዚህ ውድድር ዋዛ ሊሆን እንደማይችል ይገመታል። ውድድሩን ተከትሎ በሰጠው አስተያየትም «ይህ ትልቅ ዓመት ነው፤ በቡዳፔስቱ የዓለም ሻምፒዮና አሸናፊነቴን ለማስጠበቅ ይህ ውድድር ይረዳኛል። የእስካሁኑ ዝግጅቴ ምን ይመስላል የሚለውንም በዶሃ በሚኖረኝ ተሳትፎ መረዳት እችላለሁ» ማለቱ ለአሸናፊነት መዘጋጀቱን ያመላክታል።

በዚህ ርቀት ከለሜቻ ባሻገር ሁለት ኢትዮጵያውያን ወጣት አትሌቶችም ተሳታፊነታቸውን ያሳወቁ ሲሆን፤ ከወቅታዊ አቋማቸው በመነሳት ለአሸናፊነት የሚወዳደሩ መሆኑን መገመት አያዳግትም። ለውድድሩ ፈተና እንደሚሆኑ የሚጠበቁት እነዚህ አትሌቶችም በቶኪዮ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ሻምፒዮናው ሰለሞን ባረጋ እና በርቀቱ ስኬታማው አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ ናቸው። አትሌት ሰለሞን ባረጋ በተለይ በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች ታዋቂ ይሁን እንጂ በ3ሺ ሜትርም አስደናቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ የቻለ አትሌት ነው። በወጣቶች ቻምፒዮና ላይ ውጤታማ የሆነው ሰለሞን እአአ 2018 ላይ በበርሚንግሃም እንዲሁም ያለፈው ዓመት የቤልግሬድ የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች የብር እና የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ነው።

እአአ በ2018 በ5ሺ ሜትር የዳይመንድ ሊግ አሸናፊ የሆነው ሰለሞን በ3ሺ ሜትር ርቀት ያለው ፈጣን ሰዓትም ከክብረወሰኑ በ3 ሰከንዶች ብቻ የዘገየ ነው። ይህም አትሌቱ በዚህ ውድድርም የተለየ ቅድመ ግምት ካገኙት አትሌቶች ጋር ፉክክር በማድረግ አሸናፊነቱን የሚያሳካበት እድል መኖሩን የሚያሳይ ነው። ሌላኛው ወጣት አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻም በተመሳሳይ ከ5 እና 10ሺ ሜትር በተጓዳኝ በ3ሺ ሜትር ርቀትም ስኬትን ማጣጣም የቻለ አትሌት መሆኑ ለአሸናፊነት ተጠባቂ አድርጎታል። እአአ በ2016 በፖርትላንድ በተዘጋጀው የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና ባለ ድል ሲሆን፤ በ2018ም በርሚንግሃም ላይ አሸናፊነቱን በድጋሚ ተቀዳጅቷል። ይህም አትሌቱን ሌላኛው የዳይመንድ ሊግ ተፋላሚ ሊያደርገው ይችላል።

ለኢትዮጵያውያኑ እንዲሁም ለሞሮኳዊው አትሌት ፈተና ሊሆን እንደሚችል የተገመተውና የአሸናፊነት ቅድመ ግምቱን ካገኙት መካከል አንዱ ኬንያዊው አትሌት ቲሞታይ ቼሪዮት ነው። እአአ ከ2017 ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ዓመታት በ1ሺ500 ሜትር የዳመንድ ሊግ አሸናፊ የሆነው አትሌት ዘንድሮ ደግሞ የሚወዳደርበትን ርቀት በመቀየር ዶሃ ላይ የ3ሺ ሜትር ርቀት ተፎካካሪ ይሆናል።

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ WACHEMO UNIVERSITY
ከዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በዩኒቨርሲቲው የእንሰት ዝርያዎችን በምርምር የማውጣት ጥረት

**ዳንኤል ዘነበ**

የእንሰት ተክል በአብዛኛው የደቡብ ክልል ዞኖችና በተወሰኑ የኦሮሚያ አካባቢዎች ይመረታል። ኢትዮጵያ ውስጥ 20 ሚሊዮን ለሚሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተወዳጅ የምግብ ተክል ከመሆኑም ባሻገር የኅብረተሰቡ የክብር መገለጫም ተደርጎ ይወሰዳል። የጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሃዲያ፣ ከንባታ፣ ወላይታ ዞኖች ለረጅም ዘመናት እንሰትን በማምረት የሚጠቀሱ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በእንሰት አምራችነቱ የሚታወቀው የሃዲያ ሕዝብ ኑሮ ለረጅም ዓመታት በእንስሳት እርባታ ላይ የተመሠረተ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። የእንሰት ተክል በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በአካባቢው ከታወቁ የእርሻ ምርቶች መካከል በዋናነት ይጠቀሳል።

እንሰት በአካባቢው ቀድሞ የተዋወቀው ለዞኑ አጎራባች በሆኑት የጉራጌና የከምባታ ዞኖች መሆኑ ይነገራል። በተለይም ከ1900 እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ የአካባቢው ኅብረተሰብ የተክሉ ጠቃሚታዎች በስፋት በመረዳቱ በከፍተኛ ደረጃ ያመርተው እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ የሃዲያ ሕዝብ እንሰትን በማልማት ለምግብነት መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተክሉ ጠቀሜታ ጎልቶ እየታየው በመምጣቱ በልዩ ፍቅር ያመርተዋል። ይንከባከበዋል። ከእንሰት ምርት ከ10 በላይ የምግብ አይነቶችን ማዘጋጀት የሚቻል ሲሆን ተረፈ ምርቱን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት አለው። ለአብነትም ከእንሰት ተረፈ ምርት የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎችን ማዘጋጀት ይቻላል። አንዳንድ የተክሉ ዝርያዎች ደግሞ ለሰውና ለእንስሳት መድኃኒትነት ያገለግላሉ። እንሰት ከምግብነቱ ባሻገር ለእንስሳት መኖም ተመራጭ እንደሆን ነዋሪዎቹ ይመሰክራሉ።

**የእንሰት ምርትን**
**ለማሳደግ በማለም የተመረጡ የእንሰት ዝርያ ችግኞችን በስፋት የማፍላት ሥራ ተሠርቶ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ በሀዲያ ዞን የእንሰት አጠውልግ የሚባል በሽታ በተከሰተበት ወቅትም የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ዩኒቨርሲቲው የበሽታውን ዋና መንስኤ የመለየትና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለማፈላለግ ጥናት እያደረገ ነው**

የሃዲያ ዞን ጨምሮ በበርካታ አካባቢዎች የሚገኘው የእንሰት ተክል በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለመሆኑ የዘርፍ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ይህ ቢሆንም፤ በሀገር ደረጃ እንሰትን የሚመለከት ምንም ዓይነት የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምም ሆነ ፖሊሲ እንደሌለ ያመላክታሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በግብርና ኮሌጅ ተመራማሪ የሆኑት አቶ ዳንኤል መኖሬ (ረዳት ፕሮፌሰር) እንደሚያስረዱት፤ በዘርፍ የተደረጉ ጥናቶች እንሰት የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል ሰብል በመሆኑ በቀጣይ ጊዜያት ከሀገር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚገጥመን የምግብ ቀውስ መፍትሔ ይሆናል ሲሉ ያስቀምጣሉ። ስለዚህ የእንሰትን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ በመገንዘብ ተገቢውን ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ያስታወቁት ተመራማሪው፤ በተለይ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ አንጻር ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያደረገ መሆኑን ነው ያስታወቁት።

ዩኒቨርሲቲው ባለፉት አምስት ዓመታት ከእንሰት ተክል ጋር ተያይዞ ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች መሥራቱን ያመለከቱት ተመራማሪው፤ የእንሰት ምርትን ለማሳደግ በማለም የተመረጡ የእንሰት ዝርያ ችግኞችን በስፋት የማፍላት ሥራ ተሠርቶ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ በሀዲያ ዞን የእንሰት አጠውልግ የሚባል በሽታ በተከሰተበት ወቅትም የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ዩኒቨርሲቲው የበሽታውን ዋና መንስኤ የመለየትና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለማፈላለግ ጥናት እያደረገ ነው። ጥናቱ መሠረት በማድረግ የግብርና ሳይንስ ኮሌጅ ተመራማሪዎች ከምርምር ተቋማት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ከአከባቢው ጋር ሊላመድ (ሊስማማ) የሚችል የእንሰት ተክል ዘር ተከላ እየተካሄደ እንደሚገኝም ይገልጻሉ። “የተተከሉ እንሰት ዓይነቶች ለመድኃኒትነት፣ ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ፣ በሽታ የሚቋቋሙ እና ለአካባቢ አየር ንብረት ጥበቃ እንደሚውሉ በአምስት ዓመት የሚደርሱ ዝርያዎች ናቸው። በዋናነት ጥምር እርሻን በመሬት ለማሳየት(Agro forestry system) በተጨማሪም በዙሪያው ለተተከሉ የቡና ተክሎች ጥላ እንዲሆኑ ታስበው ሊተከሉ ችለዋል” በማለት ያብራራሉ።

በአሁኑ ወቅት በዩኒቨርሲቲው አንድ መቶ38 የእንሰት ዝርያ ተሰብስቦ ምርምር እየተሠራ ስለመሆኑ ያስታወቁት ተመራማሪው ፤ በቅርቡ ደግሞ ወደ ስምንት የሚሆን የእንሰት ዝርያ ለተጠቃሚ እንዲደርስ እንደሚደረግ ጠቅሰዋል። እነዚህ የእንሰት ዝርያዎች በምርምሩ ድርቅንና በሽታን የመቋቋም አቅማቸው፣ በምርታማነታቸው እንዲሁም በአጭር ጊዜ የሚደርሱ መሆናቸውንም ያመላክታሉ። አቶ ዳንኤል አያይዘው ዩኒቨርሲቲ ለአርሶ አደሩ የእንሰት ዝርያዎችን በምርምር ከማውጣት ባሻገር በአጠቃቀማቸው ዙሪያ የተለያዩ ሥልጠናዎች መሰጠታቸውን ይገልጻሉ።

በተጨማሪም የእንሰት ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም የማብላላት ሂደትን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎችን በአካባቢዎች ለሚገኙ እንሰት አብቃይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል። “እንሰት በአካባቢያቸው የኑሮ መሠረት እንደመሆኑ ተክሉ ለምግብነት እስኪደርስ ያለው የሥራ ሂደት በእጅጉ አድካሚ ነው። ዩኒቨርሲቲው ከኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል ጋር በመሆን አድካሚውን ሂደት ለመቀነስ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎቹን ለመሥራት የምርምር ሥራዎች እየተከናወኑ ነው” ሲሉ ነው ያስረዱት።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ